# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

81ኛ ዓመት ቁጥር 245 ግንቦት 5 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# ኢትዮጵያና ቻይና በኢንቨስትመንትና በደህንነት ዙሪያ በትብብር እንደሚሠሩ አስታወቁ

## - ሁለቱ ሃገራት የኢንቨስትመንትና የንግድ ትብብራቸውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ተስማሙ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያና ቻይና በኢንቨስትመንት፣ በንግድ፣ በሰላምና ደህንነት ዙሪያ ትኩረት ሰጥተው በትብብር እንደሚሠሩ አስታወቁ ። ሁለቱ አገራት የኢንቨስትመንትና የንግድ ተሳትፏቸውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል።

በኢትዮጵያና በቻይና መካከል ያለውን የኢንቨስትመንትና የንግድ ተሳትፎ ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን እና በኢትዮጵያ የቻይና አምባሳደር ዣኦ ዢዩአን በተገኙበት ትናንት ተፈርሟል።

በስምምነት ፊርማው ላይ የተገኙት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያና የቻይና ግንኙነት ታሪካዊና ጠንካራ ነው። ኢትዮጵያ ከቻይና ጋር በጋራ ተጠቃሚነት መርሕ ሁሉን አቀፍ ትብብርና የንግድና የኢንቨስትመንት ልውውጥ በማድረግ ከፍተኛ ለውጥ እያሳየ ነው።

የተደረገው ስምምነት የሁለቱን ሃገሮች የንግድና

ኢትዮጵያና ቻይና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ ፀሐይ ንጉሤ

አምባሳደር ዲና ሙፍቲ

# ምዕራባውያን ሃገራት ኢትዮጵያ ከሰብዓዊ እርዳታ ጋር በተያያዘ እየሠራቻቸው ያሉ ሥራዎችን ማድነቃቸው ተገለጸ

**አብዱረዛቅ መሐመድ**

ሐረማያ፡- ምዕራባውያን ሃገራትና ዓለም አቀፍ ተቋማት ኢትዮጵያ ከሰብዓዊ እርዳታ አቅርቦት ጋር በተያያዘ እየሠራቻቸው ያሉ ሥራዎችና ለሰላም ያሳየችው ቁርጠኝነት ማድነቃቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ በወቅታዊ ዲፕሎማሲያዊ ጉዳዮች ትናንት በሳምንታዊ መግለጫ ላይ እንዳሉት፥ ባሳለፍነው ሳምንት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ከአውሮፓ ኅብረት ኮሚሽን እና ከዓለም የምግብ ድርጅት ተወካዮች እንዲሁም ከዴንማርክ የልማትና የኖርዲክ ሃገራት ትብብር ሚኒስትር ጋር ውይይት አድርገዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን በኢትዮጵያ ከአሜሪካ አምባሳደር ጋር ውይይት ማድረጋቸውንም ተናግረዋል።

እንደ ቃል አቀባዩ ገለጻ፤ በኢትዮጵያ ለአውሮፓ ኅብረት ኮሚሽን አምባሳደር በድርቅና በጦርነት ለተጎዱ የኅብረተሰብ ክፍሎች እየተደረገ ስላለው የሰብዓዊ ድጋፍ፣ መንግሥት ለሰላም ባለው ቁርጠኝነት የሠራቸው በጎ ሥራዎች፣ የዜጎች የሰብዓዊ መብት አያያዝን በተመለከተ እየተሠሩ ስላሉ ሥራዎችና ተያያዥ ጉዳዮች ገለጻ የተደረገላቸው ሲሆን ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብም በበቂ

ምዕራባውያን ሃገራት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# “ለዘመናት አብሮ የኖረውን ሕዝብ በብሔርና በሃይማኖት ሽፋን ማለያየት አይቻልም”

አቶ ፒተር አማን
የጋምቤላ ክልል ፕሬዚዳንት የማኅበራዊ ጉዳይ አማካሪ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**


አዲስ አበባ፡-ለዘመናት በደምና በጋብቻ ተሳስሮና አብሮ የኖረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሃይማኖትና በብሔር ሽፋን ለማጋጨት መሞከር ይቻል ይሆናል እንጂ ማለያየት እንደማይቻል የጋምቤላ ክልል ፕሬዚዳንት የማኅበራዊ ጉዳይ አማካሪ አቶ ፒተር አማን ገለጹ፡፡

አቶ ፒተር አማን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣የኢትዮጵያ ሕዝቦች በደም፣በጋብቻና በመሰል ጉዳዮች ተሳስረው በአንድነትና በትብብር አብረው መኖር የጀመሩት ዛሬ ሳይሆን ከጥንት ጀምሮ መሆኑ ከታሪክ መረዳት ይቻላል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ

“ለዘመናት አብሮ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ ገባቦ ገብሬ



ዶክተር አርካ አቦታ

# በውሃ ጉዳይ የሚደረግ የዲፕሎማሲና የሚዲያ ሥራ ዘላቂነትና ተከታታይነት ሊኖረው እንደሚገባ ተጠቆመ

ገጽ 4


















ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሴ

አምባሳደር ዲና ሙፍቲ

## ኢትዮጵያ ከገጠማት ችግር እንድትወጣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኃላፊነት ከፍተኛ መሆኑ ተጠቆመ

### - የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ማዕከል ተቋቁሟል

**አብዱረዛቅ መሐመድ**

ሐረማያ፡- ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ኢትዮጵያ አሁን እየገጠሟት ላሉ ችግሮች ተጨባጭ መፍትሔ ሀሳብ የማቅረብ ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለባቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ገለጸ። የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ማዕከል በይፋ ተመሥርቷል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ማዕከል በይፋ ትናንት ሲመሠረት በመርሐ ግብሩ ላይ ተገኝተው እንደገለጹት፥ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሃገራችን አሁን ለደረሰችበት ሁለንተናዊ በጎ ነገሮች ሁሉ የዋሉት ውለታ እጅግ ከፍተኛ ቢሆንም ሃገሪቷ አሁን እየገጠሟት ላሉ ችግሮች ተጨባጭ መፍትሄ የማቅረብ ሃገራዊ ኃላፊነት አለባቸው።

ሃገራችን በዚህ ወቅት ከገጠሟት ዋና ዋና ችግሮች አንዱ በየጊዜው የሚሰነዘርባት ኢ-ፍትሐዊ የዲፕሎማሲ ጫናዎችና ብሔራዊ ጥቅሟን ለማሳጣት የሚሞክሩ ያልተገቡ ድርጊቶች ናቸው ያሉት ቃል አቀባዩ፤ ብሔራዊ ጥቅሞቻችንና ሃገራዊ ክብራችንን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለመጉዳት የሚጥሩ ኃይሎች እኩይ ፍላጎታቸው ለማሳካት የሚከተሉት ዋነኛ ስልት ዲጂታል ሚዲያዎችን በመጠቀም ሐሰተኛ መረጃዎችን ማሰራጨት መሆኑንም አስረድተዋል።

የሚሰነዘሩብንን ጫናዎችን ለመመከትና ብሔራዊ ጥቅማችንን ለማስጠበቅ ከምንጊዜውም በላይ ትብብርና ተቀራርቦ መሥራትን እንደሚጠይቅ ጠቅሰው፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በትብብር ለመሥራት ዘርፈ ብዙ ጥረቶችን እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

ሁሉም ዜጋ ለሃገሩ ዲፕሎማት ነው በሚል መርሕ በሁሉም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ማዕከላት እንዲቋቋሙ ተደርጓል፤ ከሐረማያ ዩኒቨርሲቲ በተጨማሪ እስካሁን በወላይታ ሶዶ፣ በቦንጋ፣ ሐዋሳ፣ አርባ ምንጭና በጎንደር ዩኒቨርሲቲዎች የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ማዕከላት በይፋ ተቋቁመዋል ብለዋል።

እነዚህ ማዕከላት በበርካታ ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ አቅም የምንፈጥርባቸው ተቋማት ናቸው ያሉት አምባሳደር ዲና፤ ለሃገራችን ዘብ የሚቆሙ ጠንካራ ዲፕሎማቶች መፍለቂያ እንዲሆኑ ተደርገው እንደሚደራጁም አስታውቀዋል።

የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደርና የተማሪዎች አገልግሎት ዘርፍ ምክትል ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ጀይላይ ወልዩ በበኩላቸው፥ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ዜጎች በሃገራቸው ያገባኛል ስሜት እንዲኖራቸው የሚያደርግ አሳታፊ የዲፕሎማሲ አይነት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ፕሮፌሰር ጀይላን ገለጻ፣ ዜጎች የሃገራቸውን ታሪክ ለማስተዋወቅ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞችን ለማስጠበቅ፣ መልካም ገጽታን ጎልቶ እንዲታይ ለማድረግ፣ ዓለም አቀፍ ተቀባይነትን ለማሳደግ እንዲሁም የሃገራቸውን ነፃነትና ሉዓላዊነት ተጠብቆ እንዲቀጥል ለማድረግ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ በጣም አስፈላጊ ነው።

ኢ-ፍትሐዊነት በነገሠበትና ሃገራት በመደበኛና ኢ-መደበኛ የዲፕሎማሲ ጫናዎች ሥር በቀላሉ እየወደቁ ባሉበት በአሁኑ ወቅት ፐብሊክ ዲፕሎማሲን ማጎልበት የሃገራትን ሕልውና የማስቀጠል ሥራ አካል ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚገባም አመልክተዋል።

# ግዙፍ የማዕድን ኩባንያዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ጥረት እያደረገ መሆኑን ሚኒስቴሩ አስታወቀ

**ሙሳ ሙሐመድ**



ኢንጂነር ታከለ ኡማ

አዲስ አበባ፡- ዓለም ላይ የሚገኙ ግዙፍ የማዕድን ኩባንያዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ለመሳብ ጥረት እያደረገ መሆኑን የማዕድን ሚኒስቴር አስታወቀ።

የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ኡማ ሰሞኑን በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያ ያላትን ዘርፈ ብዙ የማዕድን ሃብት ጥቅም ላይ ለማዋል ግዙፍ የማዕድን ኩባንያዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

የኢትዮጵያን ማዕድን ሃብት በሰፊው የማስተዋወቅ ሥራ ለተለያዩ የውጭ አገራት ከተሞች መከናወኑን ጠቁመው፤ የኢትዮጵያን የማዕድን ልማት ጉዞ ለማፋጠን በዓለም ዙሪያ አቅሙ ፣ ዕውቀቱ፣ ቴክኖሎጂው አለኝ ለሚሉ ኩባንያዎች በሚገኘው አጋጣሚ ጥሪ እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

ኢትዮጵያ በሰፊው የውጪ ማዕድናት ንግድና በአገር ውስጥ የሚመረቱ ማዕድናት እንዲሁም የኃይል ማዕድናትን በማስተዋወቅ የሃገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ዕቅድን ለማሳካት ግዙፍ የማዕድን ኩባንያዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ለመሳብ አበክራ እየሠራች ነው። በቀጣይነትም በትኩረት ትሠራለች ሲሉ ተናግረዋል።

በእስካሁኑ ጥረትም ዘርፉ ንጋት ላይ ለመሆኑም የሚያሳዩ ምልክቶች ተገኝተዋል። በተለይ ባለፉት ዓመታት በአርሲ ኢተያ የጂኦተርማል ኃይል ለማምረት እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ከመቀጠል አልፎ ከአልሚ ኩባንያ ጋር መፈራረም መቻሉም ገልጸዋል።

የአርሲ ኢተያ የጂኦተርማል ኃይል ማመንጫም ግንባታውም በሁለት ዓመት ውስጥ ተጠናቅቆ ወደ ኃይል ማመንጨት እንደሚጀምር ውጥን መያዙን ኢንጂነር ታከለ ጠቁመዋል።

በተመሳሳይ በጨውና መሰል ፋብሪካዎች ምርትና ግብይት ላይ ያተኮረ እንዲሁም የምርት ሂደቱ በዜጎች ጤና ላይ ባለው ተጽዕኖ ዙሪያ ሰፊ ሥራዎች መከናወናቸውን ገልጸዋል።

በወርቅና በተለያዩ የጌጣጌጥ ማዕድናት እንዲሁም ለፋብሪካ ግብዓት በሚሆኑ ብረትና ሌሎች ማዕድናት ዙሪያ ያለውን ሃብት ለተለያዩ ሃገራት ባለሃብቶች በማስተዋወቅ የውጭ ምንዛሪ ለመሳብ ሰፊ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ ኢንጂነር ታከለ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ የብዙ ዓይነት ማዕድን ሀብት ባለቤት በመሆኗ በተለያዩ ዘመናት ኢትዮጵያን ሲያስተዳድሩ የነበሩ አመራሮች በተለያየ መልኩ አስጠንተው ጥቅም ላይ ሊያውሉ ሞክረዋል። ዘርፉ ለሃገር ኢኮኖሚ ማበርከት ያለበትን ጥቅም ሳያበረክት ዘመናትን አስቆጥሯል። አሁን ይህን ለመቀየር የተደራጀ እንቅስቃሴ ተጀምሯል።

በሚኒስቴር ደረጃ ትላልቅ ባለሃብቶችን ለመሳብ የሚያግዝ የማዕድን ጋለሪ መዘጋጀቱን ገልጸው፤ ጋለሪው የኢትዮጵያን የማዕድን ሀብት መረጃን በቴክኖሎጂ በታገዘ መልኩ የሚያስረዳ መሆኑን ኢንጂነር ታምሩ አስረድተዋል።

ጋለሪው በኢትዮጵያ ውስጥ በማዕድን ዘርፍ ልማት ለመሠማራት ለሚፈልጉ የአገር ውስጥና የውጪ ኩባንያዎች ዋና ግብዓት መሆን እንዲችል ተደርጎ መዘጋጀቱንና ለተመራማሪዎችና ለምርምር ዘርፎችም የሚረዳ እንደሆነ ገልጸዋል።

በተለያየ ዘርፍ ላይ የተሠማሩ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችንና ከውጭ አልሚዎች የአገሪቷን ዕምቅ ኃይል ለመጠቀም የሚያስችሉ አማራጮች ላይ በየጊዜው ሰፊ ማብራሪያ እየተሰጠ ይገኛል ብለዋል።

በሃገራዊ ሪፎረሙ ረገድ ዘርፉ ለሁሉም ዘርፎች ዕድገት ወሳኙ በመሆኑ መንግሥትም ትልቅ ትኩረት አድርጎበታል፤ ከግብርና ቀጥሎ በትኩረት እየተሠራበት የሚገኘው የግብርናው ዘርፍ ነው ብለዋል።

በዘርፎ የሪፎርሙ አሠራር ለማጠናከር የሚያግዙ የማዕድን ልማት አጠቃቀምና ተያያዥ መመሪያዎችና አዋጆች መዘጋጀታቸውን አስታውሰው፤ በፋብሪካዎች አካባቢ ይነሱ የነበሩ ፍትሐዊ የጥቅም ክፍፍል፣ መሰል ጥያቄዎች ምላሽ እያገኙ እንደሚሄዱ ተናግረዋል።

# ጎንደር ዩኒቨርሲቲ “የአንድ ተማሪ ለአንድ ቤተሰብ” ፕሮጀክቱን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ገለጸ

**ፋንታነሽ ክንዴ**



ፎቶ፡ ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ፡- ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ባለፉት ዓመታት ሲተገበር የቆየው “የአንድ ተማሪ ለአንድ ቤተሰብ” ፕሮጀክቱን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ገለጸ።

አዳዲስ ተማሪዎቹን እየተቀበለ ጎን ለጎን መደበኛ የመማር ማስተማር ሂደቱን በተረጋጋ ሁኔታ እያከናወነ መሆኑን ዩኒቨርሲቲው አስታውቋል።

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ የሕዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዳይሬክተር ወይዘሮ ይዳኙ ማንደፍሮ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በትምህርት ሚኒስቴር በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ዩኒቨርሲቲው አዲስ ገቢ ተማሪዎችን ከግንቦት አንድ ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ እየተቀበለ ይገኛል።

‹‹አንድ ተማሪ ለአንድ ቤተሰብ›› በሚል በዩኒቨርሲቲው ሲተገበር የቆየው መርሐ ግብር በዚህ ዓመትም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ያስታወቁት ወይዘሮ ይዳኙ፤ በአሁኑ ወቅት ለአዳዲስ ተማሪዎቹን የሚቀበሉ ቤተሰቦችን ለመለየት የቤተሰብ ምልመላ እየተካሄደ መሆኑንና በቀጣይነት ፕሮግራም ተዘጋጅቶ የተማሪና ቤተሰብ ትውውቅ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

በፕሮጀክቱ መሠረት ወደዩኒቨርሲቲው የተመደበ ተማሪን በጎንደር ከተማ ከሚገኝ ቤተሰብ ጋር በማስተሳሰር ልክ እንደልጃቸው አስፈላጊውን እንክብካቤና ቁጥጥር እንዲያደርጉለት ይደረጋል። ይህ አሠራር በተማሪዎች ውጤታማነት ላይ መልካም ለውጥ አሳይቷል ብለዋል።

ፕሮጀክቱ ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች ምቹ፣ ሰላማዊና የተረጋጋ የምርምርና የመማሪያ አካባቢ ለመፍጠር የሚያደርገው እንቅስቃሴ አንዱ አካል መሆኑን ዳይሬክተሯ አስታውሰው፤ ተማሪዎች ተመርቀው ወደየአካባቢያቸው ሲመለሱም ከጎንደር ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዲኖራቸው ያደርጋል ሲሉ ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል ያለውን ወንድማማችነት በማጠናከር በኩልም የአንድ ተማሪ ለአንድ ቤተሰብ ፕሮጀክት ጉልህ ሚና እንዳለው ጨምረው ገልጸዋል።

ጎንደር ዩኒቨርሲቲ በዚህ ዓመት ከአምስት ሺ አምስት መቶ በላይ አዲስ ተማሪዎች ተመድበውለታል ያሉት ዳይሬክተሯ፤ ተማሪዎችን ለመቀበል ቀደም ብሎ ቅድመ ዝግጅት ሲደረግ መቆየቱን ጠቁመዋል።

አዳዲስ ተማሪዎቹን እየተቀበለ ጎን ለጎን መደበኛ የመማር ማስተማር ሂደቱን በተረጋጋ ሁኔታ እያከናወነ መሆኑን አስታውቀዋል።

በቅርቡ በከተማው ተፈጥሮ የነበረው ችግር ምንም ዓይነት ተጽዕኖ ሳያሳድርበት ዩኒቨርሲቲው የመማር ማስተማር ሂደቱ በተለመደው መልኩ ተጠናክሮ መቀጠሉንም ገልጸዋል።

በቅርቡ በከተማው ከተከሰተው ወቅታዊ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የነበረው የፀጥታ መደፍረስ እንዲረግብ ከከተማው የፀጥታ አካላት ጋር የተቀናጀ ሥራ መከናወኑን አስታውሰው፤ ከተማውም ፍፁም ሰላማዊ የዩኒቨርሲቲውም ጸጥታ የተጠበቀ በመሆኑ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲው ለመምጣት ምንም አይነት ስጋት የሚፈጥር ጉዳይ እንደሌለ አረጋግጠዋል።

ወላጆችም ልጆቻቸውን ያለምንም ስጋት በወቅቱ ወደ ዩኒቨርሲቲው በመላክ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ማድረግ አለባቸው። በቀጣይነትም በዩኒቨርሲቲው ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖር ከከተማ አስተዳደሩና ከሌሎችም የሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሠራል ብለዋል።

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ የአንድ ተማሪ ለአንድ ቤተሰብ ቃልኪዳን ፕሮጀክት ከጎንደር ከተማ አስተዳደርና ከከተማው ማኅበረሰብ ጋር በመተባበር ተግባራዊ ሲደረግ የቆየ መቆየቱ የተገለጸ ሲሆን፤ ፕሮጀክቱ በጽሕፈት ቤት ደረጃ ተቋቁሞ ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን ከዩኒቨርሲቲው የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

# “አገራዊ ፋይዳ ባለው ጉዳይ የበኩላችንን አስተዋጽኦ ማድረግ የውዴታ ግዴታችን ነው”

*- ዶክተር ንጉሱ ለገሰ*
*የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ፕሬዚዳንት*

**አዲሱ ገረመው**



አዲስ አበባ፡- በአገራዊ ምክክር ሂደቱ የሲቪል ማኅበረሰቡ ድርሻ አለው ብቻ ሳይሆን እንዲህ አይነት አገራዊ ፋይዳ ባለው ጉዳይ ውስጥ የበኩላችንን አስተዋጽዖ ማድረግ የውዴታ ግዴታችን ጭምር ነው ሲሉ የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ተናገሩ።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በመጪው አገራዊ ምክክር የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ሚና ምን መሆን እንዳለበት የሚዳስስ ውይይት አካሂደዋል። በመድረኩም የክርስቲያን በጎ አድራጎት ልማት ማኅበራት ኅብረት ዋና ዳይሬክተር እንዲሁም የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ፕሬዚዳንት፤ ዶክተር ንጉሱ ለገሰ፤ በሃገራዊ ምክክር ሂደቱ የሲቪል ማኅበረሰቡ ድርሻ አለው ብቻ ሳይሆን እንዲህ አይነት ሃገራዊ ፋይዳ ባለው ጉዳይ ውስጥ የራስን አስተዋጽዖ ማድረግ የውዴታ ግዴታችን ጭምር ነው ብለዋል።

ምክክሩ የፓርቲዎች አሊያም የጥቂት ልኂቃን ጉዳይ ብቻ እንዳልሆነ ማሳየት አንዱ ፈታኝ ሥራ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ምክክሩ ለአገር የሚበጅ ሁሉን አካታች የችግሮች መፍትሔ ፍለጋ ሂደት እንደሆነ አስታውቀዋል። በዚህ ፍለጋ ውስጥ ደግሞ የሲቪል ማኅበረሰቡ ድርሻ አለው ብቻ ሳይሆን እንዲህ አይነት ሃገራዊ ፋይዳ ባለው ሂደት ውስጥ የራሱን አስተዋጽዖ ማድረግ የውዴታ ግዴታችን ጭምር ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ዶክተር ንጉሱ፤ የዘመናት ቁስላችንን ሽረን ወደ ፊት መመልከት እንችል ዘንድ ተመካክረን አንድ ነገር ላይ መድረስ አለብን በማለት፤ በተለይ በዚህ ዙሪያ የሲቪል ማኅበራት በገለልተኛ መርሕና ተፈጥሯቸው ምክንያት ምክክሩ ተጀምሮ እስኪያበቃ ብርቱና አይተኬ ሚና እንደሚኖራቸው ገልጸዋል።

በምክክሩ የሚመጡ ምክረ ሀሳቦች ሃገሪቱ የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥታ የምትሠራባቸው ጉዳዮች ይሆኑ ዘንድ የብዙኃኑ ይሁንታ እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ ሲቪል ማኅበራት ይህ እንዲሆን እገዛ እንደሚያደርጉ አመላክተዋል። በየትኛውም ክልልና የአስተዳደር እርከን ባሉ አካባቢዎች ሁሉ በዘርፉ ያሉ ድርጅቶች ከአካባቢያቸው ማኅበረሰብ ጋር በክፉም በደጉም ጊዜያት አብረው በመሥራት ረገድ ያደራጁትን ማኅበራዊ ካፒታል መመንዘር፣ ምክክሩ እንዲሳካ የማኅበረሰቡን ንቃትና ተሳትፎ ከፍ በማድረግ ገለልተኛ ሚናቸውን መጫወት ያስችላቸዋል ነው ያሉት።

ሃገራዊ ምክክሩ ግቡ በርከት ካሉ ባለድርሻ አካላት መሐከል ብሔራዊ መግባባት መፍጠር መሆኑን በዘርፉ የታዩ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን እንደማሳያ በመግለጽ፤ ሲቪል ማኅበራት አዎንታዊ ኃይል ሆነው የምክክሩን ተዋናዮች ማገናኘት እንደሚችሉ፤ ከዚህም ባሻገር እንደ አንድ ዘርፍ ምክክሩ ውስጥ ቦታ እንደሚኖራቸውም ይሠራሉ ብለዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ረዳት ፕሮፌሰር የሆኑት ዶክተር ፈቃደ ተረፈ፤ በውይይት ሂደት ውስጥ ባለ ድርሻ አካላት በመንግሥትና በመዋቅሩ የተዋቀሩ ብቻ ሳይሆኑ ከዚህ ውጭ የሆኑ ግለሰቦችንና ቡድኖችን ያካተተ መሆን እንዳለበት በመድረኩ ተናግረዋል። ይህም ውይይቱን ተዓማኒና በተሳታፊዎች ዘንድም ቅቡልነት እንዲኖረው አጋዥ መሆኑን ጠቅሰዋል። ውጤታማ የውይይት ሂደት እንዲኖር የሲቪል ማኅበራትን ጨምሮ አካታችና ባለብዙ ያገባኛል የሚሉ አካላት ሁሉ ተሳትፎ አስፈላጊ እንደሆነም መክረዋል።

# “ሚዲያዎች በዕውቀትና በሙያው ልምድ ባላቸው ሰዎች ቢመሩ ውጤታማ ይሆናሉ”

*- ጋዜጠኛ መሰለ ገብረሕይወት*

**ዳግማዊት ግርማ**



አዲስ አበባ፡- ሚዲያዎች በዘርፉ ዕውቀትና በሙያው ልምድ ባላቸው ሰዎች መመራት ከቻሉ ውጤታማ ይሆናሉ ሲል ጋዜጠኛ መሰለ ገብረሕይወት ተናገረ።

ጋዜጠኛ መሰለ ገብረሕይወት “የሚዲያ አመራር” የተሰኘው መጽሐፉን በሚመለከት ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረገው ቆይታ እንደገለፀው፤ የሚዲያ አመራሮች በሙያው ልምድና ዕውቀት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል።

ሙያውን በአግባቡ የሚያውቁ አመራሮች ስለተቋሙ አሠራርና የመረጃ ሥርዓት በቂ ልምድ ይኖራቸዋል። ይህ ደግሞ መገናኛ ብዙኃኑን ውጤታማ እንዲሆኑና በተደራጀ መንገድ መረጃዎችን ለሕዝብ እንዲያደርሱ ያግዛል ብሏል።

ኢትዮጵያ ውስጥ በሚታየው ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ የሚዲያ አመራሮች ዘርፉን በሚገባቸው ልክ በማገልገል ላይ እንደማይገኙ የጠቆመው ጋዜጠኛ መሰለ፤ ይህም ሚዲያው በሚጠበቅበት መጠን ተፅዕኖ መፍጠር እንዳይችል ጋሬጣ ሆኖበታል ሲል ገልጿል።

ሚዲያዎችን በፖለቲካ ሹመኝነት ምደባ እንዲመሩ ከማድረግ ይልቅ ዘርፉን በአግባቡ በተረዱ ሰዎች እንዲመሩ ማድረግ ለሃገርም የሚጠቅም ለውጥ ለማምጣት ይረዳል። ሚዲያውን ውጤታማና ተጽዕኖ ፈጣሪ ለማድረግ ዕውቀት፤ ልምድና ክህሎት ላይ የተመሠረተ አካሄድን መከተል ይገባል ብሏል።

እንደ ጋዜጠኛ መሰለ ገለፃ፤ የሚዲያ አመራሮች የትምህርት ዝግጅት ሚዲያው ከሚፈልገው ጋር የማይያያዝና ዘርፉን የማያበረታታ መሆን የለበትም። በዚህ ረገድ ችግር ከተፈጠረ አጠቃላይ አሠራሩም እክል ያጋጥመዋል።

የሃገሪቱ የሚዲያዎች ችግር ዘርፈ ብዙ መሆኑን የተናገረው ጋዜጠኛ መሰለ፤ ሚዲያው ለሃገር ዕድገት ለሚኖረው ፖለቲካዊ፤ ማኅበራዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅዖ ከሚጠበቀው አንጻር እምብዛም መሆኑን ተናግሯል።

እንደ ጋዜጠኛ መሰለ ንግግር የሚዲያው ዘርፍ እንደ ኢንዱስትሪነቱ የሚገባውን ያህል ትኩረት እየተሰጠው አይደለም። ይህም ሳቢነት የሌለውና ጥራቱም የተጓደሉ ይዘት ያላቸው ዘገባዎችን በሰፊው እንዲስተዋሉ ምክንያት ሆኗል።

የመንግሥትን ሚዲያዎች ማየት ቢቻል የመንግሥትን ጥንካሬ ብቻ የሚያትቱና ለገዢው አካል እንደ አፍ በመሆን የሚያገለግሉ ዘገባዎችን ብቻ ሲዘግቡ፤ በተቃራኒው የግል መገናኛ ብዙኃንም የመንግሥትን ድካም ብቻ እየተከታተሉ መዘገባቸው ዘርፉን በእጅጉ እየጎዳ እንደሚገኝም ጋዜጠኛው ጠቁሟል።

ይህንንና መሰል ችግሮችን ለማረቅ በሚል በሚዲያ አመራርነት ላይ ያተኮረ መጽሐፍ ማዘጋጀቱን ገልጾ፤ መጽሐፉ የሚዲያ አመራሮች ክህሎት ምን መሆን አለበት? ሚዲያ ሙያዊ በሆነ መንገድ እንዴት ይመራል? አንድ የሚዲያ ተቋም ከሌላ ተቋማት ምን የተለየ መንገድ አለው የሚሉትና መሰል መሠረታዊ ጉዳዮችን እንደሚዳስስም ጋዜጠኛ መሰለ ገብረሕይወት ተናግሯል።

መጽሐፉን የረዥም ዓመት የሥራ ልምዱንና በትምህርት የቀሰመውን ዕውቀት በማዋሓድ ያዘጋጀው እንደሆነ የገለጸው ጋዜጠኛ መሰለ፤ መጽሐፉ በጋዜጠኝነት ትምህርት እንዲሁም በሚዲያ አመራር ዘርፍ ላይ የራሱ አስተዋጽዖ እንደሚኖረውም እምነቱ መሆኑን ተናግሯል።

የሚዲያ አመራር በሚል ርዕስ በጋዜጠኛ መሰለ ገብረሕይወት የተዘጋጀው መጽሐፍ ከትላንት በስቲያ ተመርቋል። መፅሐፉ 323 ገፆች ያሉት ሲሆን፤ በ13 ምዕራፎች ተሰንዷል።



አቶ ሳንዱካን ደበበ

# ኢንዱስትሪ ፓርኮች 113 ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚያወጣ ምርት ለሃገር ውስጥ ገበያ አቅርበዋል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ኢንዱስትሪ ፓርኮች ባለፉት ዘጠኝ ወራት 113 ሚሊዮን 527 ሺህ 035 ዶላር የሚያወጣ ምርት ለሃገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ መቻላቸውን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ገለፀ። ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ አምርተው ወደ ውጭ ከላኳቸው ምርቶችም 152 ሚሊዮን 766 ሺህ 261 የአሜሪካን ዶላር መገኘቱንም ተመልክቷል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሳንዱካን ደበበ ትናንት ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ኢንዱስትሪ ፓርኮች በ2014 በጀት ዓመት ባለፉት ዘጠኝ ወራት 113 ሚሊዮን 527 ሺህ 035 ዶላር የሚያወጣ ምርት ለሃገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ ችለዋል።

በተለይ ለኢንቨስትመንትና ለኢንዱስትሪዎች የአለፉት ወራት አስቸጋሪዎች እንደነበሩ የገለፁት ዋና ሥራ አስፈፃሚው፤ ምንም እንኳን በተወሰኑ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ከጦርነቱ ጋር በተያያዘ አስቸጋሪ ሁኔታ ቢያጋጥምም ችግሮችን ተቋቁሞ በአመዛኙ ውጤታማ ሥራ መሠራቱን ጠቁመዋል።

ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ አምርተው ለውጭ ገበያ ከአቀረቧቸው ምርቶችም 152 ሚሊዮን 766 ሺህ 261 የአሜሪካን ዶላር መገኘቱን ጠቅሰው፤ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለባለሀብቶች በኪራይ ከተላለፉ 135 ሼዶች ውስጥ 98 የሚሆኑት ማምረት መጀመራቸውም ተናግረዋል።

ከተላለፉት 98 ሼዶች 37 ሼዶች በተሟላ መልኩ እያመረቱ አይደለም ያሉት አቶ ሳንዶካን፤ ይህ የሆነበት ምክንያት ሼዶችን ተረክበው ወደ ሥራ የገቡ ባለሀብቶች በተወሰኑ ሼዶች ላይ ብቻ ሥራ መጀመራቸውና የመቐሌ ኢንዱስትሪ ፓርክ በወቅታዊ ችግር ምክንያት ፓርኩ ያለበት ሁኔታ አስቸጋሪ መሆኑ አውስተዋል።

በበጀት ዓመቱ ከሼዶች፣ ከለማ መሬት ኪራይና ከምክርና ሥልጠና አገልግሎት እንዲሁም ከቢዝነስ ልማት ሥራዎች እና ሌሎች ገቢዎች 791 ሚሊዮን 417 ሺህ 371 ብር ማግኘት መቻሉንም ሥራ አስፈፃሚው ገልፀዋል።

በተመሳሳይ በ2014 በጀት ዓመት ባለፉት ዘጠኝ ወራት ወደ ሥራ ከገቡ ኢንዱስትሪ ፓርኮች 44 ሺህ 292 የሥራ ዕድል መፈጠሩን የገለፁት አቶ ሳንዱካን፤ ከተፈጠሩ የሥራ ዕድሎች ሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ እና አዳማ ከፍተኛውን ደረጃ ይዘዋል ብለዋል። የሥራ ዕድል ፈጠራው ከአለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር ከሰባት በመቶ በላይ ዕድገት ማስመዝገቡንም ተናግረዋል።

ይህም ሊሆን የቻለው በበጀት ዓመቱ ምንም እንኳን በተለያዩ አካባቢዎች ለኢንዱስትሪዎች ምቹ ያልሆነ ሁኔታ ቢኖርም በአዳማ፣ በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርኮች እና አዲስ ኢንዱስትሪ መንደር ውስጥ ያሉ ባለሀብቶች ከፍተኛ የሆነ የሰው ኃይል በመቅጠራቸው እንዲሁም የቂሊንጦና ባሕር ዳር ኢንዱስትሪ ፓርኮች ወደሥራ መግባታቸው ለተፈጠረው የሥራ ዕድል መፈጠር መሻሻል አስተዋፅዖ አድርገዋል ተብሏል።

በአሁኑ ጊዜም በበጀት ዓመቱ ከተፈጠረው ጋር ተዳምሮ በአጠቃላይ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ከ76 ሺህ በላይ ዜጎች የሥራ ዕድል እንደተፈጠረላቸው ታውቋል።

ዜና

# በውሃ ጉዳይ የሚደረግ የዲፕሎማሲና የሚዲያ ሥራ ዘላቂነትና ተከታታይነት ሲኖረው እንደሚገባ ተጠቆመ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በውሃ ጉዳይ የሚደረግ የዲፕሎማሲ እና የሚዲያ ስራ ዘላቂነት እና ተከታታይነት ያለው ሊሆን እንደሚገባ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን መምህር ዶክተር አርካ አቦታ ገለጹ።

ዶክተር አርካ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በውሃ ጉዳይ የሚደረግ የዲፕሎማሲ እና የሚዲያ ሥራ ዘላቂነት እና ተከታታይነት ሊኖረው ይገባል። የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች በውሃ ጉዳይ አሠራራቸውን ማሻሻልና ማዘመንም ይጠበቅባቸዋል።

የዲፕሎማሲና የሚዲያ ሥራው ‹‹ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ›› አይነት ነው። ይህ መለወጥ ይኖርበታል ያሉት ዶክተር አርካ፤ በአንድ ወቅት ለሚከሰት ነገር ከማሟሟቅና ከማጋጋል አካሄድ ወጥቶ ተከታታይነት እና ዘላቂነት ባለው መንገድ ሊሠራ ይገባል ብለዋል።


ለተግባሩ ሁሉም ዜጋ በተለይ ደግሞ ዲያስፖራው ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ሊሠራ እንደሚገባ ያመለከቱት ዶክተር አርካ፤ የግብጽ ዲፕሎማሲ ከጥንት ጀምሮ የማጥቃትን ሂደት ይከተላል። የዲፕሎማሲ አሠራር ዘዴ ኢትዮጵያ ከምትከተለው አሠራር ጋር ሲነጻጸር አይገናኝም። የኢትዮጵያም የዲፕሎማሲ አካሄድ መለወጥ ይኖርበታል ብለዋል።

ግብጾች በዓለም ላይ የአሜሪካና የአውሮፓ ቁልፍ ላይ የሚገኙ ሰዎችን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚገኙ ትላልቅ የገንዘብ ተቋማትንም ይዘዋል።

ግብጾች ኢኮኖሚያቸው የተሻለ ስለነበር በአንዳንድ የገንዘብ ተቋማት ውስጥ የገንዘብ ድርሻ አላቸው። ከዚህ የተነሳ ግብፃውያን የመቀጠር ዕድል ተሰጥቷቸዋል። እነዚህ ሰዎች ለደመወዝ ሳይሆን የግብጽን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ይታገላሉ።

እንደርሳቸው ገለጻ፤ የኢትዮጵያና የግብጽ የውሃ ዲፕሎማሲ በምንም አይገናኝም። ‹‹የናይል ውሃ ከግብጽ ደጋማ ተራራ ይመነጫል›› ብለው በሐሰት መረጃ ዓለምን ያሳመኑ ሰዎች ናቸው። ኢትዮጵያ እውነታው እያላት ከማስተባበል የዘለለ ሥራ አልሠራችም።

ግብጾች ለዓላማቸው እስከጠቀማቸው፣ ብሔራዊ ፍላጎታቸውንም እስካሟላላቸው ድረስ ሺህ ጊዜ ይዋሻሉ። አልቻሉም እንጂ ፍላጎታቸው የነበረው ውሸቱን እውነት አድርገው ዓለምን በማሳሳት ውሃውን በብቸኝነት



ዶክተር አርካ አቦታ

መጠቀም ነበር።

የኢትዮጵያ የውሃ ዲፕሎማሲና የሚዲያ ሥራ ተወዳዳሪ መሆን እንደሚኖርበት ገልጸው፤ የታላቁ ህዳሴ ግድብን ለማልማት የኢትዮጵያ መንግሥት ብድር ባጣበት ወቅት ሕዝቡ በጋለ ስሜት በመነሳሳት በማዋጣቱ ለአሁኑ ስኬት መብቃት ችሏል። ሚዲያው ይህንን በማስተባበር ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። አሁንም ሚዲያው ሕዝብን በማንቃትና በማነሳሳት ሚናው ሊቀጥል እንደሚገባ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ እሺ ብላ የማትገዛ በመሆኗም የውጭ ኃይሎች አይወዷትም ያሉት ዶክተር አርካ፤ ሌሎች የአፍሪካ ሃገራትን አልገዛም ማለትን በማስተማር ታሳድምብናለች በሚል ስጋትም የተለያዩ ተጽእኖዎችን ያደርጉባታል ብለዋል።

የሰላም ችግር ልማትን ለማሳደግ፣ የተፈጥሮ ሃብትን ለማልማት እንቅፋት የሚፈጥር በመሆኑ መንግሥት ከሕዝብ የተቀበለውን ሰላም የማስጠበቅ ኃላፊነትና አደራ በአግባቡ ሊወጣ ይገባል። ይህንን በመገንዘብ ሕዝቡም አንድነትን ማጠናከር ይገባዋል። አሁንም ሚዲያው ሕዝብን በማንቃትና በማነሳሳት ሚናው ሊቀጥል ይገባዋል።ምክንያቱም የዲፕሎማሲው ሥራ ውጤታማ የሚሆነው የሃገር ውስጡ ሰላምና አንድነት ሲጠናከር መሆኑን ጠቁመዋል።

# ኢትዮጵያና ቻይና…

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የኢንቨስትመንት ልውውጥ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የሚያስችል መሆኑን አመልክተው፤ በሁለቱ ሃገራት የተፈጸመው አዲስ የኢንቨስትመንትና የንግድ ልውውጥ ስምምነት ትልቅ ትርጉም አለው። ለዚህ ስኬት የኢትዮጵያ መንግሥት በቁርጠኝነት እንደሚሠራና ለስኬቱም የአስተዳደርና የፋይናንስ ተቋማት በቅንጅት መሥራት አለባቸው ብለዋል።

በኢትዮጵያ የቻይና አምባሳደር ዣኦ ዢዩአን በበኩላቸው፣ በቻይናው ፕሬዚዳንት ዠ ፒንግ በቻይና አፍሪካ ትብብር የሚተገበሩ ዘጠኝ ፕሮግራሞች ይፋ መደረጋቸውን አስታውሰው፣ ቻይና በምስራቅ አፍሪካ ሰላምና ዕድገት እንዲረጋገጥ በመንገድ፣ በኢኮኖሚ ሪፎርምና በቻይና ኢትዮጵያ መካከል ጠንካራ የሆነ የሁለትዮሽ ግንኙነት እንዲዳብር ቻይና እንደምትሠራ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የጀመረችውን የብልጽግና ጉዞ ለማረጋገጥ በምታደርገው ጉዞ ቻይና በሰላምና ደህንነት፣ በልማት፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በማኅበራዊ ዘርፍ ጠንካራ የሆነ ሁሉን አቀፍ ትብብር በመመሥረት እንደምትሠራ አምባሳደሩ ተናግረዋል።

ትናንት በተደረገው ስምምነት በተጨማሪ አምስት በሚደርሱ ኩባንያዎች መካከል የስምምነት ፊርማ ተደርጓል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ለሊሴ ነሜ በስምምነት ፊርማው እንደገለጹት፣ ኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንት ምቹና ተስማሚ ናት፣ በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ ጊዜው አሁን ነው።

የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን በማስተዋወቅና በማስፋፋት የአገሪቱን ኢኮኖሚ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ከተለያዩ ሃገራት ጋር ግንኙነቱን በማጠናከር የኢንቨስትመንት ዘርፉን ለማሳደግ እየሠራ ነው ብለዋል።

በሁለቱ አገራት መካከል የተደረገው ስምምነት፣ የቻይና መንግሥት ባለሀብቶቹ በኢትዮጵያ የተለያዩ ዘርፎች ላይ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጠርና ኢትዮጵያም ለባለሀብቶቹ አማራጮችን እንድታቀርብ የሚያስችል መሆኑን ኮሚሽነሯ ተናግረዋል።

የመግባቢያ ስምምነቱ መፈረም ኢትዮጵያ ለጀመረችው ኢኮኖሚያዊ ግስጋሴ የአቅም ግንባታ እና ሌሎች ድጋፎችን ለማድረግ እንደሚያግዝ የገለጹት ኮሚሽነር ሌሊሴ፤ ስምምነቱ የኢትዮጵያና የቻይና መንግሥታት፣ የቻይና ባለሀብቶች በተለየ ሁኔታ በኢትዮጵያ መዋለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ የሚያደርግ ነው ብለዋል።

የቻይና የኢንቨስትመንትና ፕሮሞሽን ኤጀንሲ ዳይሬክተር ጀነራል ያንግ ሂንግ በዙም በመታገዝ ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፣ በኢትዮጵያ ከ400 በላይ የቻይና ኩባንያዎች በኮንስትራክሽን፣ ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ በግብርና፣ በማዕድን ዘርፍ፣ በአገልግሎት፣ በመሠረተ ልማት፣ በአይሲቲ፣ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የኢንቨስትመንት አማራጮች ላይ እየተሳተፉ ነው። ስምምነቱ ይህን አጠናክሮ ለማስቀጠል ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ነው።

ኢትዮጵያ ወደ ቻይና ከላከችው ምርቶች የተገኘው የውጭ ምንዛሪ እ.ኤ.አ በ2021 በፊት ከነበሩት ዓመታት በስምንት በመቶ አድጓል። ኢትዮጵያ ከቻይና ኩባንያዎች በቀጥታ ኢንቨስትመንት የምታገኘው በ364 በመቶ ያደገ ሲሆን የአሁኑ ስምምነት ዕድገቱን በ25 በመቶ ከፍ እንዲል ያደርገዋል ብለዋል።

እንደ ያንግ ሂንግ ገለጻ፤ ኢትዮጵያና ቻይና ጠንካራ የሆነ የረጅም ዓመታት የኢንቨስትመንት ግንኙነት አላቸው። ቻይና በኢትዮጵያ ለምታደርገው ኢንቨስትመንት ልዩ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች ነው።በሁለቱ ሃገሮች መካከል ያለው ሁለትዮሽ ኢኮኖሚዊና ማኅበራዊ ግንኙነት እያደገ መጥቷል ።

የቻይና ባለሃብቶች በኢትዮጵያ በኢንቨስትመንት ዘርፍ በከፍተኛ ደረጃ እንዲሳተፉ የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ በኢንቨስትመንት ኮሚሽነሯና በቻይና ኢንቨስትመንትና ፕሮሞሽን ዳይሬክተር መካከል ተፈርሟል።

አሁን ባለው ሁኔታ ኢትዮጵያ ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት ከምታገኝባቸው ቀዳሚ ሃገራት መካከል ቻይና ቀዳሚ አገር መሆኑ ይታወቃል።

# ምዕራባውያን…

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሁኔታ የሰብዓዊ እርዳታ እንዲያቀርብም ተጠይቀዋል።

የአውሮፓ ኅብረት ኮሚሽን የኢትዮጵያ ተወካይ ኢትዮጵያ እያደረገችው ስላለው ጥረት ምስጋናቸውን አቅርበዋል ያሉት ቃል አቀባዩ፤ ኢትዮጵያ ከሱዳን ጋር የገባችበትን የድንበር ውዝግብ በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት አቋም መያዟን የሚደገፍ ነው ማለታቸውም ጠቁመዋል።

አቶ ደመቀ መኮንን ከዴንማርክ የልማትና የኖርዲክ ሃገራት ትብብር ሚኒስትር ጋር ውይይት ማድረጋቸው የገለጹት አምባሳደር ዲና፤ የኢትዮጵያ መንግሥት በሃገሪቱ ሰላምን ለማምጣት እያደረጋቸው ስላሉ ጥረቶች በተመለከተ ለሚኒስትሩ ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል ብለዋል።

ሚኒስትሩም የኢትዮጵያ መንግሥት በሁሉም ዘርፎች እያደረጋቸው ያሉ ጥረቶች አበረታች ናቸው ማለታቸውን አምባሳደር ዲና አስታውቀዋል።

እንደ አምባሳደር ዲና ገለጻ፣ አቶ ደመቀ ከዓለም የምግብ ድርጅት የኢትዮጵያ ተወካይ ጋር ውይይት ያደረጉ ሲሆን ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በድርቅና በጦርነት የተጎዱ 20 ሚሊየን ዜጎች ለመታደግ እየሠራች መሆኗን ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል፤ ድርጅቱም ለኢትዮጵያ እያደረገው ያለውን የሰብዓዊ እርዳታ አጠናክሮ እንዲቀጥልም ጠይቀዋል።

ተወካዩ ኢትዮጵያ የሰብዓዊ እርዳታዎችን ተደራሽ ከማድረግ አንጻር እየሠራቻቸው ያሉ ሥራዎችንም አድንቀዋል ብለዋል።

በተጨማሪም፣ ተወካዩ ኢትዮጵያ ውስጥ ከዘጠኝ መቶ ሺህ በላይ የውጭ ሃገራት ስደተኞች እንዳሉና ኢትዮጵያ አስፈላጊውን እንክብካቤ እያደረገች መሆኗን አመልክተው፤ የዓለም የምግብ ድርጅት በኢትዮጵያ እያከናወናቸው ያሉ ሥራዎችን ለማጠናከር ቃል መግባታቸውን ገልጸዋል።

በሌላ በኩል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ከአሜሪካ አምባሳደር ጋር በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ መወያየታቸው የገለጹት አምባሳደር ዲና፤ መንግሥት ለሰላም በጎ እርምጃ እየወሰደ ባለበት ወቅት አሸባሪው ሕወሓት አሁንም ትንኮሳዎችን እየፈጸመ በመሆኑ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ጫና ሊያደርግበት እንደሚገባ መጠየቃቸውን አስረድተዋል።

የአሜሪካ አምባሳደር በበኩላቸው የኢትዮጵያ መንግሥት የሚያደርጋቸውን ጥረቶች ለመደገፍ የአሜሪካ መንግሥት አስፈላጊውን ትብብር እንደሚያደርግ ቃል መግባታቸውን ቃል አቀባዩ አብራርተዋል።

# "ለዘመናት አብሮ የኖረውን…

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ግን በፖለቲካ ነጋዴዎች አማካኝነት ለዘመናት አብሮ የኖረውን ሕዝብ በብሔርና በሃይማኖት ሽፋን ለማጋጨት ቢሞከርም መለያየት ግን ፈጽሞ አይቻልም።

የፖለቲካ ነጋዴዎች በሃይማኖትና በብሔር ሽፋን ግጭት በመጠንሰስና በመፍጠር ለብዙ ሰዎች ሕይወት መጥፋትና ለንብረት ውድመት መንስኤ መሆናቸውን አመልክተው፤የኢትዮጵያ ሕዝብ በፖለቲካ ነጋዴዎች የሚደረገውን አፍራሽ ቅስቀሳን በማጋለጥና በማምከን የቆየ ለአብሮነቱን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚኖርበት አመልክተዋል።

እንደ አቶ ፕቴር ገለጻ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የእብድ ገላጋይ ሆኖ ለፖለቲካ ነጋዴዎች ዱላ አቀባይ እንዳይሆን ነገሮችን በጥልቀት ማጤን ይጠበቅበታል። የትኛውም ወገን ከግጭት ኪሳራ እንጂ ትርፍ ስለማያገኝ የወንድሙ ሰላም ጠባቂ መሆን አለበት። አንድነትና አብሮነት ለኢትዮጵያ የኩራት ምንጭ እንጂ የሥጋት ሆኖ አያውቅም፤ ለወደፊትም ለዘመናት የዘለቀው አብሮነትና አንድነት ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት መልካም እሴታችን ነው።

እንደየትኛውም አገር በአትዮጵያ ግጭት ሊከሰት ይችላል ያሉት አቶ ፕቴር፤ የቀደሙት አባቶቻችን የሚፈጠሩ ግጭቶችን በእርቅ እየፈቱና ዘላቂ መፍትሔ እያበጁ በመቻቻል በጋራ አገር እንዳስቀጠሉት ሁሉ ዛሬም በአብሮነትና አንድነትን በማጠናከር አገር ማስቀጠል እንደሚገባ ገልጸዋል።

በሃገሪቱ እየተስተዋሉ ያሉ ግጭቶችና በዩክሬንና በራሽያ ጦርነት ምክንያት በሃገሪቱ የኑሮ ውድነት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ማሳረፉን ገልጸው፤ በሰላም ወጥቶ ለመግባትና ገቢን ለማሳደግ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በብሔርና በሃይማኖት ሳይከፋፈል የወንድማማችነትና የአብሮነት ስሜት እንዲላበስም ጠይቀዋል።

የጋምቤላ ክልል ኢትዮጵያውያን ይቅር የግሪክና የጣሊያን ዜጎች ሳይቀር አግብተውና ተዋልደው ያለምንም የፀጥታ ሥጋት የሚኖሩበት መሆኑን የተናገሩት አቶ ፕቴር፣ ምንም እንኳ አንዱ ሌላውን ለማፈናቀልና ለማሳደድ የሚያደርገው የጥላቻ ቅስቀሳዎች ለክልሉ ፈተና ቢሆኑም በአሁኑ ጊዜ አንጻራዊ መሻሻሎች መኖራቸውን አመልክተዋል።

በክልሉ ከሁሉም አካባቢዎች የመጡ ዜጎች አብረው የሚኖሩበት በመሆኑ ጋምቤላ "ትንሿ ኢትዮጵያ" በመባል እንደምትታወቅ የጠቆሙት አቶ ፕቴር፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የፖለቲካ ነጋዴዎች የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሕዝቦቹን ለማጋጨት ያቀዱት ሴራ በሕዝቡና በጸጥታ ኃይሎች ጋር ቅንጅት በተሠራው ሥራ አመርቂ ውጤት መታየቱን አስገንዝበዋል።

አሁን ባለው ሁኔታ በጋምቤላ ክልል ሕዝቦችን የማጋጨት ሴራ አሳሳቢ ጉዳይ ባይሆንም በክልሉ የሚገኙ ስደተኞችና በተለያዩ ጊዜያት ድንበር አቋርጠው ሰርገው በመግባት ሕጻናትን የሚያግቱና ከብቶችን የሚዘርፉ ከሙርሌ ታጣቂዎች መኖራቸውን አመልክተው፤የፌዴራልና የክልሉ ፀጥታ አካላት በቅንጅት በመሥራታቸው የሚሰነዘር ጥቃት መመከት መቻላቸውንና አሁንም በጉዳዩ ላይ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ምስጋናም የዝግጁነት ማሳያም!

ኢትዮጵያ ለሕይወታቸው ሳይሳሱ፣ የግል ኑሯቸው ሳያሳስባቸው የህይወት መስዋእትነት እየከፈሉ በህልውናዋ ላይ የተጋረጡ ፈተናዎችን፣ ውጣ ውረዶችን፣ አደጋዎችን ለማለፍ ያስቻሏትን የጦር ግንባር ባለውለታዎቿን ማሰብን ፣ ማመስገንን፣ እውቅና መስጠትን ባህል እያደረገች መጥታለች፡፡

አሸባሪው ሕወሓት በአማራና አፋር ክልል ፈጽሞት የነበረውን ወረራ ለመቀልበስ በተደረገው የህልውና ዘመቻ የተመዘገበውን ታላቅ ድል ተከትሎ በየመከላከያ ሰራዊቱ እዞች፣ ማሰልጠኛዎች፣ ወዘተ ሲሰጡ የቆዩ የእውቅናና ምስጋና እንዲሁም የማእረግ እድገት መስጠት መርሀ ግብሮችን ለዚህ በአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

በባህርዳር ከተማ ከትናንት በስቲያ ለጸጥታ ሃይሎች የተሰጠው የእውቅናና የምስጋና መርሀ ግብርም ሌላው የእውቅናና ምስጋናው ማሳያ ነው፡፡ አሸባሪው ሕወሓት ኃይል በወረራ ይዟቸው ከቆየ የአፋርና አማራ ክልል አካባቢዎች ዋጋ ከፍሎ እንዲወጣ ያስቻለ ድል በመጎናጸፍ የጸጥታ ኃይሎች የፈጸሙት ተጋድሎ ታላቅ ነበርና የምስጋናና እውቅና መርሀ ግብሩም ታላቅ የሚባል ነው፡፡

በዚህ ታላቅ ሥነ ሥርዓቱ ላይ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ኢትዮጵያ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ባለችበት ወቅት ራሳቸውን ለአገራቸው አሳልፈው የሰጡትን ማስታወስ፣ ማወደስ ማመስገንና ለሌሎች አርአያ እንዲሆኑ ማድረግ መታደል ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡ ከአሸባሪው ሕወሓት ጋር በተካሄደው ውጊያ መከላከያ፣ የፌዴራል ፖሊስ፣ ልዩ ኃይሎችና፣ ልዩ ልዩ መጠሪያ ያላቸውና የተለያዩ ዩኒፎርሞችን የለበሱ ኃይሎች በአንድነት ተሰልፈው ጠላትን ማሳፈርና የሀገሪቱን ነጻነት ማስቀጠል እንደቻሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረው፣ በእለቱ የተሰጠው ሽልማት የህይወት እና የደም ዋጋ ለከፈሉ እንዲሁም በገንዘብና በእውቀት ለሀገራቸው አስተዋጽኦ ላበረከቱት መላ ኢትዮጵያውያን የተሰጠ መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለውም የእውቅናና ምስጋና መርሀ ግብሩ ሰፊ መሆኑን ነው፡፡ በህልውና ዘመቻው ውጊያው የተካሄደው በጦር ግንባር ብቻ አልነበረም፤ በኢኮኖሚውና በሌሎችም ዘርፎችም ተካሂዷል፡፡ በመከላከያ ሠራዊት ብቻም አልተካሄደም፤ የተለያዩ የጸጥታ ሀይሎች ተሳትፈውበታል፡፡ እውቅናና ምስጋናው እነዚህን ሁሉ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በገንዘብና በእውቀት ድጋፍ ላደረጉ ኢትዮጵያውያውን በሙሉ የተሰጠ ታላቅ ምስጋናና እውቅናም ሊባል ይችላል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት እነኚህን ጀግኖች ማመስገን በእርግጥም መታደል ነው፡፡ መተኪያ የሌላትን ውድ ህይወት በመሰዋት የሀገርን ህልውና ከሀገር ውስጥና ከውጭ ታሪካዊ ጠላቶች መታደግ ከምንም በላይ ትልቅ ክብር ሊሰጠው ይገባልና ምስጋናውም ትልቅ ነው፡፡

የእውቅናና ምስጋና መርሀ ግብሩ ፋይዳ ከምስጋናና እውቅናም ይዘላል፡፡ የመንግሥትን የክተት ጥሪ ተቀብሎ ወደ ወታደራዊ ማሰልጠኛዎች፣ ግንባሮች የተመመ ወገን ባስመዘገበው ታላቅ ድል ማግስት ማመስገንና እውቅና መስጠት ለሀገሩ የከፈለውን ውድ ዋጋ ክብር መስጠት እንዲሁም የጸጥታ ሀይሉን አይቀላቀሉም ሲባሉ የነበሩ ወጣቶች የጸጥታ ኃይሉን እንዲቀላቀሉና በቀጣይ እልፍ ጀግኖችን ለማፍራትም ይጠቅማል፡፡

ኢትዮጵያ ጠላቶቿ መቼም ተኝተውላት አያውቁም፤ ተሸንፈው እንደ እባብ አፈር እየላሱ የሚነሱ እንዲሁም የጭቃ ውስጥ እሾህ የሆኑ ጠላቶችም አሉባት፡፡ መንግሥት ለሀገር የሚበጀው ሀገራዊ መግባባት መፍጠር መሆኑን አምኖ ለእዚህ ተግባራዊነት ኮሚሽን አቋቁሞ ኮሚሽነሮች ተሰይመው እየሰሩ ባለበት በአሁኑ ወቅት ጭር ሲል የማይወደው ትህነግ በህልውና ዘመቻው ድል ተመትቶ ትግራይ ውስጥ ተወሽቆ በተላላኪዎቹ ኢትዮጵያን ሲወጋ ቆይቷል፤ አሁን ድግሞ የጦርነት ነጋሪት እየጎሰመ ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን በብሄር ፣ በሃይማኖት፣ በጎሳ፣ ወዘተ እንዲከፋፈሉ የእድሜውን ያህል የሰራው ትህነግ ዛሬም በተላላኪዎቹ ጭምር ሀገር ለማተራመስ እየሰራ ነው፡፡ እነዚህ ኃይሎች ዜጎችን በሃይማኖት፣ በጎሳ፣ በብሄር ወዘተ በመከፋፈል፣ ግጭት በመቀስቀስና በማባላት ላይ ተጠምደዋል፡፡

አሸባሪው ሕወሓት ዛሬም ከስህተቱ አልማር ብሎ ጦርነት እየደገሰ ነው፡፡ ባካሄዳቸው ጦርነቶችና ወረራዎች የገበረው የትግራይ አንድ ትውልድ አልበቃው ብሎት፣ በአማራና በአፋር ክልል ወረራ ፈጽሞ ያደረሰው ታሪክ ይቅር የማይለው ጥፋት ፣ በመላ ኢትዮጵያ እዚህም እዚያም ግጭት በመቀስቀስ የፈጸመው ነውር አልበቃ ብሎት በጦርነት ድግስ ላይ መጠመዱ፣ መሳሪያ ማወዛወዙ አሁንም የትም እንደማያደርሰው መረዳት አልፈለገም፤ ወይም ከአፈርኩ አይመልሰኝ ብሎ ቀጥሎበታል፡፡

ይህም ወቅቱን የተለየና ወሳኝ ያደርገዋል፤ በዚህ ወቅት ጀግኖችን መሸለምና እውቅና መስጠት ለጀግኖቹ እና ለመላ ኢትዮጵያውያንም አደራ መስጠት ይሆናል፡፡ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ጠላቶች ጠንካራ መልእክት ማስተላለፍም ነው፡፡

በአሸባሪው ሕወሓት ላይ ከተካሄደው የህልውና ዘመቻና ከተገኘው ድል መረዳት እንደሚቻለው ኢትዮጵያውያን የጀግኖች አባት እናቶቻቸውን ድል ደግመዋል፡፡ አንድ ላይ ሆነው የማይፈጥሩት ተአምር እንደሌለ በድጋሚ ማሳየት ችለዋል፡፡ ይህ ለጠላቶቻችን በቂ ትምህርት የሚሰጥ ቢሆንም፣ መማር የማይፈልጉና አርፈው የማይቀመጡ ጠላቶቻችንን ልክ ለማስገባት ዝግጁነት ላይ መስራት ይገባል፡፡ ኢትዮጵያውያን አሁንም ይህን ጠላት ለማንበርከክ አብረው መስራታቸውን ማጠናከር እንዳለባቸው ያስገነዝባል፡፡

ኢትዮጵያውያን የአሸባሪው ሕወሓት ተላላኪዎቹን የጥፋት አላማ የተረዱ እንደመሆናቸው የጠላቶቻቸው ሴራ ጠልፎ እንደማይጥላቸው በህግ ማስከበር ዘመቻውም በህልውና ዘመቻውም፣ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በተቀሰቀሱ ግጭቶችና ጦርነቶች ሁሉ የጠላትን ሴራ በመበጣጠስ አረጋግጠዋል፡፡ የብሄር፣ የሃይማኖት፣ የጎሳ ልዩነቶች ውበት እንጂ የሚባሉባቸው አለመሆናቸውን አሳይተዋል፡፡ ልዩነቶቻቸው ለኢትዮጵያ ከመዋደቅ አላገዳቸውም።

ወደፊትም የሚሆነው ይሄው ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ሁሉም የጸጥታ ኃይሎች በተሻለ አቋምና ብቃት ላይ እንደሚገኙ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አስታውቀዋል፡፡ የጸጥታ ሀይሎች ዝግጁነት አንድ ጉዳይ ነው፡፡ የሀገሪቱን ጠላቶች ለማስተንፈስ እና በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት የኢትዮጵያውያን ዝግጁት ያስፈልጋል፡፡

የጸጥታ ኃይሉ ደጀን ሕዝብ መሆኑ በሚገባ ይታወቃል፡፡ ህዝብ አብሮነቱን አሁንም በተጨባጭ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ የአሸባሪው ሕወሓትና ተላላኪዎቹ መሳሪያ ላለመሆን ጥረት ከማድረግ በተጨማሪ በተሰማራበት መስክ ውጤታማ ሥራ በመስራት ሀገሩ የምትጠብቅበትን መፈጸም ይኖርበታል፡፡ በእያንዳንዱ ኮሽታ ባለመደናገጥ፣ ራሱንና ሀገሩን ከሀገሪቱ ጠላቶችና ተላላኪዎቻቸው በመጠበቅ የጀግና የፀጥታ ኃይል ደጀን መሆኑን ማረጋገጥም ይኖርበታል!

ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በጋራ ታግለን መመስገናችን፣ ነገም በጋራ ሰርተን የመበልጸጋችን ማሳያ ነው

**በየኔነው ስሻው**

ከውስጥ በሚነሱም ሆነ ከውጪ ለወረራ በሚመጡ ጠላቶች ምክንያት አገር ሕልውናዋ አደጋ ላይ ሲወድቅ፤ በዚህም የሕዝብ ክብርና አብሮነት ለፈተና ሲጋለጥ፤ የአገር ሕልውና እንዲጠበቅ፣ የሕዝቦችም ክብርና አብሮነት እንዲዘልቅ በዘመናት ሂደት ውስጥ አያሌ መስዋዕትነቶች ተከፍለዋል፡፡ ኢትዮጵያም ከሦስት ሺህ በዘለለው የአገረ መንግስትነት ጉዞዋ መሰል ችግሮች ተደጋግመው ገጥመዋት፤ በልጆቿ መስዋዕትነት የውጭ ወራሪን አሳፍራ፣ የውስጥ ባንዳና አገር ሻጭን አደብ አስይዛ አንድነቷን ጠብቃ፣ ታፍራና ተከብራ ዛሬ ላይ ደርሳለች፡፡

በዚህ መልኩ ሕልውናዋን ለማስጠበቅ፤ የዜጎቿን ክብር ለማስቀጠል በተደረገ ትግል ደግሞ አያሌ ጀግኖች ተፈጥረዋል። ለአገርና ሕዝብ ቅድሚያ የሰጡ የቁርጥ ቀን ልጆቿም ከፍ ያለ መስዋዕትነት ከፍለዋል፡ ፡ ኢትዮጵያም ከሃዲዎችን የምትቀጣ ብቻ ሳትሆን፤ ለክብሯ የወደቀላትን የማትረሳና ጀግኖቿን የምታከብር ናትና፤ ወራሪን አሳፍረው፣ ባንዳን አደብ አስይዘው ከፍ ያደረጓትን ጀግኖቿን ከፍ ስታደርግ፤ ስታመሰግን፣ እውቅና ስትሰጥና ስትሸልም ኖራለች፡፡

ይህች ታላቅ እና የጀግና ምድር ኢትዮጵያ ታዲያ፤ ገናን ስሟ እንዲጠለሽ፣ ስልጣኔዋ እንዲሟሸሽ፣ የከፍታ ጉዟዋ እንዲገታ የሚፈልጉ በርካቶች እንደመሆናቸው በየዘመናቱ የሚተናኮሳት የውስጥም የውጭም ጠላት አታጣም፡፡ በቅርቡም አገር ሻጭ ተላላኪ አሸባሪዎቹ ሕወሓት እና ሸኔ የፈጸሙት ክህደትም የዚሁ እውነት ማሳያ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ታሪክ ራሱን ሲደግም ደግሞ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ይሄን ክህደት የወለደው የአሸባሪ ሃይሎች አገር የማፍረስና የሕዝቦችን ክብር አዋርዶ አንድነታቸውን የመንጠቅ ክፉ ሕልም በአንድ ቆመው ማምከን ቻሉ፡፡

ኢትዮጵያም አፍራሾቿን ማፍረስ ብቻ ሳይሆን፤ ጠባቂዎቿን ማበርታት፣ ጀግኖቿን መሸለም ታውቅበታለችና ለሕልውናዋ የተዋደቁላትን፣ ለክብሯ የሞቱላትን አስባለች፤ ሸልማለች፣ ከፍ አድርጋም አሳድጋለች፡፡ በዚህ ረገድ ለጀግናው የመከላከያ ሠራዊት አባላትና አመራሮች በየደረጃው የተሰጠው እውቅናና የማዕረግ እድገት ቀዳሚው ሲሆን፤ እንደየአበርክቷቸው ለሚዲያ ተቋማት፣ ለሲቪል ማህበራት፣ ለጤና ባለሙያዎች፣… የተሰጠው ክብርና እውቅና አገር ባለውለታዎቿን ትናንትም ዛሬም የማትዘነጋ ስለመሆኗ ሕያው ምስክር የሚሆን ተግባር ነው፡፡

ሰሞኑንም በባህር ዳር ከተማ "በሕግ ማስከበር እና በሕልውና ዘመቻ የተከፈለ መስዋእትነት ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት እና አንድነት" በሚል በተካሄደ የእውቅናና ምስጋና መርሃ ግብር ይሄው ጀግኖችን የማስታወስ፤ ባለውለታዎችን የማሰብ፣ በክብር ስለ አገርና ሕዝባቸው ራሳቸውን መስዋዕት ያደረጉትን የመዘከር አገራዊ ባህል ውጤት ነው፡፡ በመሪ ሀሳቡ እንደተመላከተውም፤ አሸባሪው ሕወሓት አገርን የማፍረስ ተልዕኮውን እውን ለማድረግ የአገር ጋሻ ሆነው በኖሩት በሰሜን እዝ የመከላከያ ሰራዊት አባላት ላይ የፈጸመውን ጥቃት ተከትሎ፤ ስለ ኢትዮጵያ ክብርና ስለ ሕዝቦቿ አንድነት ሲሉ በሕግ ማስከበር ዘመቻው አያሌ ልጆቿ ዋጋ ከፍለዋል፡፡

የሕግ ማስከበር ርምጃው በቀናት ውስጥ በድል ከተጠናቀቀ በኋላ ለሰብዓዊነት ቅድሚያ በመስጠት መከላከያ ሰራዊቱ ከትግራይ ክልል እንዲወጣ በተደረገ ማግስት፤ የሽብር ቡድኑ ዳግም የባንዳነት ተልዕኮውን ለመወጣት ወደ አማራ እና አፋር ክልሎች ለወረራ በመሰማራት እስከ ሰሜን ሸዋ ዘልቆ የጥፋት በትሩን አሳረፈ፡፡ ይሄ ደግሞ የአገርንም ሕዝብንም የሕልውና አደጋ ውስጥ የከተተ እንደመሆኑ የቁርጥ ቀን ልጆቿ ዳግም ለመስዋእትነት ተሰልፈው ተላላኪዎችን ድል በመንሳት እንደ ቀድሞው ሁሉ በመስዋእትነታቸው ሕልውናዋን አስጠበቁ፡፡ ዛሬም ድረስ ይሄው ቡድን የሚያደርገውን ትንኮሳ የማክሸፍ፤ በቀጣይ ሊፈጽም የሚፈልገው ነገር ካለም በማያዳግም መልኩ ለመቅጣት በሙሉ ዝግጁነት ላይ መሆናቸው እየታየ ነው፡፡

በዚህ መልኩ አገርንም ሆነ ሕዝብን ከሕልውና ስጋት ነጻ ያወጡ እነዚህ የአገር የቁርጥ ቀን ልጆች ያለ ልዩነት በአንድ ተሰልፈው ዋጋ እንደከፈሉ ሁሉ፤ ድላቸውንም በአንድነት አጣጥመዋል፡፡ ዛሬም የጋራ መስዋዕትነታቸው ውጤት የሆነውን የምስጋናና እውቅና መርሃ ግብር በጋራ ታድመው፤ በጋራ ተመስግነዋል፤ ተሸልመዋልም፡፡ ይህ ምስጋጋና እውቅና ለአገር ሕልውና ሲባል የተከፈለን ከፍ ያለ ዋጋ ለማሰብ ብቻም አይደለም፤ ይልቁንም ቀጣይ ለሚፈጠሩ አገራዊ ስጋቶችና ፈተናዎችም የኖረ አንድነትን ጠብቆ በጋራ መሰለፍና መሻገር የሚያስችል ሙሉ ዝግጁነትን ስለመያዝ ማሳሰቢያና ይሄንኑ የማድረግ ኃላፊነትን የመስጠትም ጭምር እንጂ፡፡

በዚህ መልኩ የሚሰጥ እውቅናና ምስጋናን ተከትሎ የሚጠበቅ ታላቅ ኃላፊነትን የመቀበል ባህል ለኢትዮጵያውያን አዲስ ባይሆንም፤ ዛሬ ላይ ግን ከእውቅናው ባሻገር ያለው አደራ ቃል የመቀበል ኃላፊነት በእጅጉ ከፍ ያለ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡ ፡ ምክንያቱም የዛሬዋ ኢትዮጵያ በውስጥም በውጪም ከፍ ያሉ ፈተናዎች ያሉባት፤ አያሌ ጠላቶች ትኩረት ያደረጉባት፤ ዜጎቿን የመከፋፈልና የማባላት ተልዕኮን አንግበው የሚንቀሳቀሱ አሸባሪና ጽንፈኛ ኃይሎች ያቆጠቆጡባት ናት፡፡ ከዚህ ምስጋጋና እውቅና ማግስት የምንወጣው ኃላፊነትም እነዚህን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ተገንዝበና ይሄንን ለመሻገር የሚያስችለንን ሕብረት ፈጥሮ በመጓዝ ነው፡፡

ኢትዮጵያን ሁሉን አቀፍ ወደ ሆነ ብልጽግና እናደርሳታለን ሲባል፤ ወደ ብልጽግናው ለመሻገር የሚያስችሉ አቅሞችን አሰባስቦ መስራትና በሂደቱ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በአሸናፊነት መወጣትን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ ሁለንተናዊ ብልጽግናው እውን የሚሆነው ደግሞ የአገር ሰላምና ሉዓላዊነትን ማረጋገጥ፤ የዜጎችን ገብቶ የመውጣት ሕልውና ማስጠበቅ፤ የኑሮ ጫናን ከዜጎች አቅም በላይ እንዳይሆን ማድረግ፤ ተነጋግሮ የመግባባት ባህልን አጎልብቶ በሕብረት የመቆም መሰረትን ማጠንከር፤ ከምንም በፊት ለአገር እና ሕዝብ ከፍታ ቅድሚያ ሰጥቶ መስራት ሲቻል ነው፡፡

ይሄን ማድረግ እንደሚቻል፤ ችግሮቻችንንና ፈተናዎቻችንን አሸንፈን የመሻገር አቅም እንዳለን ደግሞ የሩቅም የቅርብም ጉዟችን ሕያው ምስክር ነው፡፡ መመስገናችንም ይሄንኑ በማድረጋችን ነው፡፡ በቀጣይም ይሄንኑ አድርገን የአገራችንን ሕልውና አስጠብቀን፤ ሁሉን አቀፍ ብልጽግናችንን ከማረጋገጥ የሚያግደን ነገር ይኖራል የሚል እምነት የለኝም፡፡ ይህ እንዲሆን ግን ከምንም በፊት የቀደመውን ሂደታችንን እያየን፣ የቀጣይ መዳረሻችንን እያሰብን ከልዩነቶቻችን ይልቅ ለድሎቻችን ትኩረት መስጠት ይጠበቅብናል፡፡ ይሄን ስናደርግና ለዚሁ ተግተን በጋራ መሰለፍ ስንችል፤ ትናንትም ሆነ ዛሬ በጋራ ታግለን እንደተመሰገንን ሁሉ፤ ነገም በጋራ ሰርተን መበልጸግ እንደምንችል በተግባር እናረጋግጣለን፡፡

## ነፃ ሃሳብ

# የአገር ባለአደራ ወጣቶች

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ዛሬ ለአገር ስለሚጠቅሙ አስፈላጊ ወጣቶች እናወራለን። አገር የምትፈልጋቸው ወጣቶች ምን ዓይነት እንደሆኑ እናወጋለን። እስኪ ልጠይቃችሁ አገራችን ናት ያልተመቸችን ወይስ እኛ ነን ያልተመቸናት? ይሄን ጥያቄ በመመለስ ቀጣዩን ጽሑፍ እንድታነቡ እጋብዛችኋለሁ። ቀደም ብዬ ያነሳሁትን ጥያቄ በራሴ አተያይ ለመመለስ ያህል፤ ለአገራችን ያልተመቸናት እኛ ነን ባይ ነኝ። እኛ ለአገራችን ብንመች አገራችን ለእኛ የማትመችበት ምንም ምክንያት አይኖርም። እሷ የአባቶቻችን ሀቅ ናት። እሷ የደጋግ ልቦች ስፍራ ናት። እሷ የነምኒልክ፣ የነአብዲሳ አጋ፣ የነዘርዐይደረስ ርስት ናት። እኛ እንጂ እሷ ውሸት ሆና አታውቅም።

አገር እኮ የእኔና የእናንተ አስተሳሰብ ናት። በተዛባ አስተሳሰብ የፈጠርናትን አገራችንን አትመችም ብሎ ማሰብ ፍርደ ገምደል ያስብላል እንጂ ጀብድ አይሰጥም። ከዓለም ሀቆች አንዱ የትኛውም ሕዝብ በአንድ ልብ፣ በአንድ ሀሳብ ከቆመ አገሩን እንደሚፈልገው አድርጎ መሥራት ይችላል የሚለው ነው። ብዙዎቻችን ወደ አገራችን ጣታችንን የምንቀስር ነን። እንደምታውቁት አገራችን ኢትዮጵያ ከአገሬው ሕዝብ ከፍ ያለ ቁጥር የያዘ ወጣት ካለባቸው የዓለም አገራት ውስጥ አንዷ ናት። ግን በሚፈለገው መልኩ ወጣቱ በአገር ጉዳይ ላይ የነቃ ተሳትፎ ሲያደርግ አይታይም።

የአገሬ ሰው ወጣትነትን ከኃይል ጋር ሲያቆራኘው ‹ወጣት የነብር ጣት› ይላል። ወጣትነት የኃይል፣ ለውጥ፣ የብርታት አብራክ ነው። ያለምንም ጥርጥር ወጣትነት በአንድ አገር ላይ ሕዝብ የሚፈልገው፣ መንግሥት የሚፈልገው፣ ትውልድ የሚፈልገው የኃይል ሞገድ ነው። ወይም ደግሞ ለአንድ አገር ዋልታና ማገር ነው ብለን በአጭሩ ልንገልጸው እንችላለን። አሁን ላይ በኢኮኖሚ አቅማቸው የዓለምን ስልጣኔ በበላይነት የሚመሩ አገራት አንድ ወቅት ላይ ወጣቶቻቸውን የተጠቀሙ ናቸው። በተቃራኒው ደግሞ በኢኮኖሚ ኋላ የቀሩ አገራት የወጣት ኃይላቸውን ሳይጠቀሙ ያለፉ እንደሆነ መገመት አይከብድም።

አገራችን ኢትዮጵያ በጉያዋ ብዙ ወጣቶችን ታቅፋ በመካንነት የምትኖር አገር ናት። የወጣቱን ኃይል፣ እውቀትና ጊዜ የሚፈልጉ በርካታ ማህበራዊ አገልግሎቶች ቢኖሩም በተፈለገው መልኩ ጥቅም ላይ ሲውል የሚታይ የወጣት ኃይል የለም። አብዛኛው ወጣት ሥራ ፈጥሮ ከመሥራት ይልቅ የመንግሥትን እጅ የሚጠብቅ ነው። አብዛኛው ወጣት በሱስና በማይጠቅመው ነገር ጊዜውን የሚያጠፋ ነው። አብዛኛው ወጣት ሠርቶ ከመለወጥ ይልቅ በአቋራጭ መበልጸግን የሚናፍቅ ነው። አብዛኛው ወጣት በእውቀትና በምክንያታዊ ሀሳብ ከመኖር ይልቅ በስሜት የሚነዳ ነው። እንደዚህ ዓይነት ወጣቶች ለአገርና ወገን ሸክም ከመሆን ባለፈ ለአገር የሚፈይዱት አንዳች ነገር የለም።

አገር ራዕይ ያለው ወጣት ትፈልጋለች። የሚሠሩ እጆች፣ በቅንነት የተሞሉ ልቦች ትሻለች። አገራችን ኢትዮጵያ ይሄን ሁሉ ወጣት ይዛ ለምን ድሀ የሆነች ይመስላችኋል? በአንድ አገር ላይ የሕዝብ ቁጥር ወይም የወጣት መብዛት ብቻውን ዋጋ የለውም። እጅ መሥራት ካልለመደ፣ አእምሮ ማሰብ ካልጀመረ፣ ልብ ትህትናን ካልተማረ የወጣት መኖር ብቻውን ጥቅም የለውም። ወጣት ኃይልና ብልጽግና የሚሆነው ከስንፍና ወጥቶ መሥራት ሲጀምር ነው። ተምሮ ሥራ ከመጠበቅ ሥራ ፈጥሮ ለሌሎች ዕድል መፍጠር ሲቻል ነው።

አሁን ላይ በሕዝብ ቁጥራቸው አነስተኛ ሆነው በኢኮኖሚ አቅማቸው የበለጸጉ ብዙ አገራት ሞልተዋል። እኚህ አገራት ምንም ተዐምር አልሠሩም የወጣት ኃይላቸውን በአግባቡ ነው የተጠቀሙት። ዋናው የሕዝብ ቁጥር መብዛት ሳይሆን የሕዝብ የሥራ ባህል ነው። የሥራ ባህል ባልዳበረባት አገር ላይ የወጣት መብዛት ብቻውን ችግር እንጂ መፍትሄ አይሆንም። የአገራችን ወቅታዊ ችግርም ከዚህ የዘለለ አይደለም። የተማሩ ብዙ ወጣቶች አሉን፤ ግን የመንግሥትን እጅ የሚጠብቁ ናቸው። ብዙ ወጣቶች አሉን፤ ግን ሥራ ፈጥሮ ለመሥራት የሰነፉ ናቸው። ብዙ ወጣቶች አሉን ግን ብዙ ጊዜአቸውን በሱስና በማይጠቅም ነገር ላይ የሚያሳልፉ ናቸው።

አገር የምትፈልጋቸው ወጣቶች ብርሃናማ ናቸው። በራዕይ የተሞሉ፤ ከትንሽ ነገር ተነስተው ትልቅ ቦታ

> **ዋናው የሕዝብ ቁጥር መብዛት ሳይሆን የሕዝብ የሥራ ባህል ነው። የሥራ ባህል ባልዳበረባት አገር ላይ የወጣት መብዛት ብቻውን ችግር እንጂ መፍትሄ አይሆንም። የአገራችን ወቅታዊ ችግርም ከዚህ የዘለለ አይደለም። የተማሩ ብዙ ወጣቶች አሉን፤ ግን የመንግሥትን እጅ የሚጠብቁ ናቸው። ብዙ ወጣቶች አሉን፤ ግን ሥራ ፈጥሮ ለመሥራት የሰነፉ ናቸው። ብዙ ወጣቶች አሉን ግን ብዙ ጊዜአቸውን በሱስና በማይጠቅም ነገር ላይ የሚያሳልፉ ናቸው**

ለመድረስ የሚታትሩ እንዲህ ናቸው። ይሄን ጽሑፍ የምታነቡ ወጣቶች አገራችሁ የእናንተን ኃይል የእናንተን እውቀት ትፈልጋለችና ለአገራችሁና ለሕዝባችሁ መልካም ነገር ለመሥራት ትጉ። የነገዋ የኢትዮጵያ ተስፋ በእናንተ እጅ ውስጥ ነው። ብዙ ያደረገላችሁን አገርና ሕዝብ ለማገዝ ትክክለኛ ጊዜ ላይ ናችሁና ከስንፍና ወጥታችሁ ወደ ልማት ግቡ። ዘረኝነት ለእናንተ አይመጥንም። ሱስና አልባሌ ነገር ጊዜአችሁን ከማባከን ባለፈ የሚሰጣችሁ ትርፍ የለም። ከትንሽ ነገር ተነስታችሁ ትልቅ ነገር መስራት ይቻላችኋል። ሁሉም ትልቅ ነገር ከትንሽ የተጀመረ ነው። ሁሉም ስኬታማ ሰው ከምንምነት የተነሳ ነው።

በእርግጥ ውስጣቸው አንድ ኃይል ነበር። እርሱም ስኬታማ የመሆን ጽኑ ፍላጎት ነው። እርሱም አገር የመለወጥ ጽኑ ምኞት ነው። ጽኑ ፍላጎት ካላችሁ እመኑኝ የፈለጋችሁትን መሆን ትችላላችሁ። ብዙዎቻችን ራዕይ አልባ ነን። በወጣትነታችን ውስጥ ለአገር የሚሆን ምንም የለም። ይሄ ደግሞ ወደ ፊት እንዳንሄድ የሚከለክለን አደገኛ ነገር ነው። መጀመሪያ የሁሉም ነገር መሠረት የሆነውን ራዕይ ልበሱ። ከዚያም ወደ ፈለጋችሁበት መሄድ ትችላላችሁ። ህልማችሁ ሀብታም መሆን ከሆነ፣ ህልማችሁ ገንዘብ ማግኘት ከሆነ፣ ህልማችሁ ቤትና መኪና ከሆነ በህልማችሁ በኩል የምታገኙት ነውና ይቻላችኋል። ሆኖም ራዕይ ገንዘብን መፍጠር ሲችል፤ ገንዘብ ግን ሁልጊዜ ራዕይን መፍጠር ይቸግረዋል።

ሁሉ ነገር እንዲኖራችሁ ከሁሉ አስቀድማችሁ መልካም ራዕይን የእናንተ አድርጉ። ከሁሉ በፊት የአገር ፍቅር ስሜትን ውረሱ። ራዕይና የአገር ፍቅር ስሜት አንድ ላይ ሲገናኙ ተዐምር የመፍጠር ኃይል አላቸው። በውስጣችን ከሁለት አንዱ ከጎደለ ግን የምንፈልገውን እኛን መሆን አይቻለንም። የዓለምን ተጽእኖ ፈጣሪ ሰዎች ታሪክ ብትበረብሩ ባለራዕይና በአገር ፍቅር ያበዱ ሆነው ታገኟቸኋላችሁ። መጀመሪያ በአገር ፍቅር ስሜት እበዱ፤ በአገር ፍቅር ስሜት ስናብድ ርምጃችን ሁሉ አገር ወደሚጠቅም፣ ትውልድ ወደ ሚቀርጽ ነው የሚሆነው። በአገር ፍቅር ስሜት ስናብድ ሌሎችን ከማፍቀርና ከመውደድ ሌላ ለአልባሌ ነገር የሚሆን ጊዜ አይኖረንም። እንደ ወጣት ወጣቱን የምመክረው እንዲህ ነው፤ በአገር ፍቅር ስሜት እንዲያብድ።

ሰው አገሩን ሲያፈቅር ትህትናን ነው የሚማረው። ድሀ ወገኑን ከችግር ለማውጣት ራዕይ ነው የሚሰንቀው። የዚህ ዘመን ወጣት ትልቁ ችግራችን እንደ አባቶቻችን ያለ አስተማሪና በጸጋ የተሞላ ነፍስና ልብ በዙሪያችን ማጣታችን ነው። በዙሪያችን ያለው ነገር ሁሉ ለመለያየት፣ ተስፋ ለመቁረጥ መንገድ የሚከፍት ነው። ገንዘብ እያላቸው ራዕይ የሌላቸው ሰዎች አታውቁም? እኔ ግን አውቃለሁ። የምትፈልጉትን የሚሰጣችሁ ራዕያችሁ ነው። ራዕይ ያለው ዜጋ በመሆን የአገራችሁን ትንሳኤ እንድታበስሩ እለምናችኋለሁ። በወጣቱ ዘንድ በብዛት የተለመደውና ጥንካሬአቸውን የሚያጡበት አንዱና ዋነኛው ነገር ምንም የለኝም የሚል አፍራሽ አመለካከት ነው። ትልቅ የሚሆኑት ትንንሽ ነገሮች እንደሆኑ ገና አልገባንም። በአንድ ጊዜ ትልቅ ነገር የምንመኝ ነን። ትላልቅ ነገሮች የተቀመጡት ደግሞ ለሚሠሩና ለሚሞክሩ ነው።

አጠገባችን ያለን ትንሽ ነገር ወደ ትልቅ የሚለውጥ ህልምና ራዕይ ያስፈልጋል። ውስጣችን ለመለወጥ የሚሆን በቂ ራዕይ ስለሌለ ሁልጊዜ ሰበበኞች ነን። ልባም ሰው ሰበብ አይፈልግም። ተነስቶ ይሠራል እንጂ። የቁጥሮች መጀመሪያ ዜሮ አይደል? ዜሮ የሌለበት ትልቅ ቁጥር ታውቃላችሁ? ትልቅ ነገር ከፈለጋችሁ ከዜሮ ጀምሩ፤ ከምንምነት ተነሱ። ታላቅ ነገር ያለው ምንምነት ውስጥ ነው። ለምሳሌ ብናይ ሊንደን ጆንሰን የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ከመሆናቸው በፊት ያልሠሩት ሥራ አልነበረም። በልጅነታቸው ጫማ ጠርገዋል፣ የጽዳት ሥራ ሠርተዋል፣ ሳህን አጥበዋል፣ አትክልተኛ ሆነው ሠርተው ነበር። በእኛም አገር ከትንሽ ነገር ተነስተው ትልቅ ቦታ የደረሱ በርካታ ሰዎችን አውቃለሁ።

እናንተም ህልማችሁ ማደግና መለወጥ ከሆነ አሁን ካላችሁበት ቦታ ላይ ተነስታችሁ የምትፈልጉትን መሆን ትችላላችሁ። ለምንም ነገር ህልማችሁ ይቅደም። ለምንም ነገር የአገር ፍቅር ስሜታችሁ ይቅደም። የምንፈልገው ድንቅ ነገር ሁሉ ህልማችንን ተከትሎ የሚመጣ ነው። መጀመሪያ ከሱስ እንውጣ። መጀመሪያ ከዘረኝነት ነፃ እንሁን። መጀመሪያ ለአባቶቻችን ሥርዓት እንገዛ። መጀመሪያ የተማረ ሳይሆን የተባረከ ትውልድ ለመሆን እንጣር። ውስጣችን ሳይጠራ፣ አስተሳሰባችን ሳይስተካከል የምናሳካው ጥሩ ነገር የለም። በራዕይና በአገር ፍቅር የታጀበ ለድሀ ሕዝብ የሚሆን ጥሩ ሀሳብና ጥሩ ምኞት ይኑረን። በራዕይ መኖር ስልጣኔ ነው። በዚህ ስልጡን ዘመን ላይ እየኖርን ጊዜን በማይጠቅም ነገር ላይ እንደማሳለፍ የሚቆጭ ምንም ነገር የለም። ጊዜው ለራሳችንም ለሌሎችም መልካም ሥራ የምንሠራበት ወቅት ነው። ዝም ብሎ ከመኖር መውጣት አለብን። እስካሁን ለራሳችንም ለአገራችንም ሳንበጅ በከንቱ የኖርንበት ጊዜ ነበር። ከእንግዲህ ግን በዋጋ መኖር አለብን። ለአገር ስጋት ከመሆን ወጥተን ክብርና ኩራት ወደመሆን መሸጋገር አለብን።

የምንደክመውም የማንበረታውም በውስጣችን ተስፋ ሲጠፋ ነው። በውስጣችን ተስፋቢስ ስንሆን በሕይወታችንም ተስፋ ቢስ እንሆናለን። በውስጣችን ስንበረታ በዓለምም እንበረታለን። ይሄ ማለት ነጋችን የሚፈጠረው በእኛው አስተሳሰብ ልክ ነው ማለት ነው። ብሩህ ነገ እንዲኖረን ብሩህ አስተሳሰብ ሊኖረን ግድ ይላል። ከአይሳካልኝም አስተሳሰብ ወጥተን ወደ ይቻላል፤ ወደ ይሳካልኛል ሀሳብ መምጣት አለብን። ለዚህም ወጣቶች ኃይላችሁን መግደል የለባችሁም። አገራችንን ሳንጦራት፣ ለቁም ነገር ያበቃንን ድሀ ወገናችንን ሳንደግፍ ወጣትነታችን እንዳያልፍ እንፍራ። ድህነት የማይንደው፣ ችግር የማይበግረው ከተስፋ መቁረጥ ከፍ ያለ የይቻላል መንፈስን በውስጣችን እንገንባ። ለመለወጥ ከተሰናዳን መለወጥ ይቻለናል። ምንም ነገር ለማድረግ ኃይሉ አለን። የወጣትነት ዕድላችንን ከተጠቀምን የማንፈነቅለው የድህነት ቋጥኝ አይኖርም።

የሕይወት ትልቁ ጸጸት በተሰጠን ዕድሜ ተጠቅመን ለራሳችንም ሆነ ለሌሎች የሚጠቅም በጎ ሥራ ሳንሰራ ማለፍ ነው። በዚህ የወጣትነት ዘመናችን፣ በዚህ የጉብዝና ጊዜአችን በድህነት ላይ የበላይ ሆነን አገራችንን ከኋላ ቀርነት ማላቀቅ ከሁላችን የሚጠበቅ የቤት ሥራ ነው። ምክንያቱም ዛሬ አገር ካለ እኛ ማንም የላትም፤ የአገራችን ተስፋ እኛ ወጣቶች ነን። የምንሰጣት ካልሆነ የምትሰጠን ምንም የላትም። የምናደርግላት ካልሆነ የምታደርግልን አንዳች የላትም። ኃይላችንን ተጠቅመን ለራሳችሁም ሆነ ለአገራችን በጎ ነገር ለመሥራት መትጋት ይኖርብናል። እንደ ዜጋ በአካልም ሆነ በአእምሮም ተሠርቶ ያለቀ ማንነት ያስፈልገናል። ስኬት ራሳቸውን ላዘጋጁ ሰዎች የተቀመጠ እንደመሆኑም ለምንም ነገር የተዘጋጀን ልንሆን ይገባል።

ስኬት እየወደቁ መነሳት ነው፤ ወድቆ መቅረት ግን አይደለም። እየደከሙ መበርታት ነው፤ ደክሞ መቅረት ግን አይደለም። የተሸነፉ መስሎ ማሸነፍ ነው፤ ተሸንፎ መቅረት ግን አይደለም። ስኬት መንገድ ነው፤ መድረሻ የሌለው ጥግ አልባ የሕይወት ህልቆ መሳፍርት። እንደ ወጣት ራዕይ ከሌለን መነሻም መድረሻም አይኖረንም። የመኖርን ትርጉም የምንረዳው በራዕይ በኩል አልፈን ስንኖር ብቻ ነው። ለዚች ዓለም ምን ያክል አስፈላጊዎች እንደሆንን የምንረዳው ዋጋ ያለን እንደሆንን ሲገባን ነው። መልካም ነገር ያለው በመራመድ ውስጥ፣ በመሞከር ውስጥ ነው። እጃችንን አጣጥፈን በመቀመጥ ለራሳችንም ሆነ ለድሀ አገራችን የምንጨምረው ነገር የለም። ካልሠራን፣ ካልሞከርን ድህነትን ምርጫ አድርገን እንደተቀበልን ማወቅ አለብን።

በትጋት ያልታጀበ ወጣትነት ነገ ላይ ጸጸት ይጠብቀዋል። ምንም ነገር ለማድረግ ትክክለኛው ጊዜአችን አሁን ነው። ሁሉን የሚሰጠን መኖራችን ሳይሆን በመኖራችን ውስጥ የምንገነባው ታላቅ የመለወጥ ፍላጎት ነው። በምክንያት በታጀበ እውቀት ፍላጎታችን እንዲመራን መፍቀድ እንጂ ለድህነት እጅ ሰጥተን መቀመጥ አርነት አያወጣንም። ከድንግዝግዝ ሕይወት ወጥተን ለአገራችን የሚሆን ብርሃንን እናመንጭ። በሌሎች ብርሃን ለመኖር አትሞክሩ ሌሎች በእናንተ ብርሃን እንዲመላለሱ ሆናችሁ ወጣትነታችሁን በዋጋ ኑሩት። ለስኬት ተብሎ የተፈጠረ የተለየ ቀን የለም ራዕይ ያላቸው ሁሉ ለስኬት የተፈጠሩ ናቸው። ስኬት በራዕይ የሚፈጠር የጽኑ ፍላጎት ፍጻሜ ነው። ምንም ነገር ለማድረግ የምትጠብቁት ጊዜ አይኑር።

ለመለወጥ ፍላጎት ካላችሁ አሁኑኑ መለወጥ ይቻላችኋል። እኛ ከተለወጥን የማይለወጥ ምንም ነገር የለም። ሁሉም ነገር ልክ ሊሆን የእኛን መለወጥ እየጠበቀ ነው። ለውጥ በዕድሜ መጨመር ሳይሆን በአስተሳሰብ መላቅ፣ በአእምሮ መበልጸግ ነው። ለውጣችሁን የአእምሮ እንጂ የአካልና የዕድሜ ለውጥ አታድርጉት። በአእምሮ ካልጎለመሳችሁ፣ በአስተሳሰብ ካበረታችሁ የአካል ጉልምስናችሁ ምንም ነው። ለውጣችሁ ያለው በማሰባችሁ ውስጥ ነው። የነገ ብሩህ ቀናችሁ ያለው በአእምሯችሁ ውስጥ ነው። ከእስራታችሁ ወጥታችሁ አገራችሁ የምትፈልጋችሁ ጥሩ ዜጋ ሁኑ።

በአካል ጎልምሰው በአእምሮ የደከሙ በርካታ ወጣቶች በዙሪያችን አሉ። እነዚህ ወጣቶች በአካላቸው የሚያስቡ፣ በፈርጣማ ጡንቻቸው የሚመኩ እንስሳዎች ናቸው። ጥሩ ከማሰብ ይልቅ ጥሩ የጸጉር ቁርጦችን በመቆረጥ ጭንቅላታቸውን የሚያሳምሩ እንዲህም ናቸው። ጭንቅላት የአሁኑን ዓለም ያስገኘ የለውጥ ማዕከል ሲሆን አካል ደግሞ የሚታየውን ዓለም የሚያጠፋ የድንቁርና ጥግ ነው። ብዙዎቻችን ከአንገት በላይ ውበት ያለ አይመስለንም። አሳራችንን የምናየው ለገጻችን ነው። ውበት ከጭንቅላት እንደሚወጣ ገና አልገባንም። ውበት ጥሩ ማሰብ ነው። ውበት በራዕይ መኖር ነው። ህልምና ራዕይ የሌለው ሰውነት ውበት የለውም። ውበታችሁን ራዕያችሁ ውስጥ ፈልጉት። አገራችን የምትፈልገን ታማኝ ዜጋ በመሆን የበኩላችንን እንወጣ እያልኩ ላብቃ። ሰላም!

# ‹‹የላምበረት ልጆች ለላምበረት ነዋሪዎች››

አስናቀ ፀጋዬ

ደስታንም ሆነ ኀዘንን ተካፍሎ መኖር የቆየ የኢትዮጵያውያን ባህል ነው። በችግር ጊዜ መረዳዳትም ከትውልድ ትውልድ ተሻግሮ የመጣ የኢትዮጵያውያን እሴት ነው። ይህ መረዳዳትና ኀዘንንና ደስታን ተካፍሎ መኖር ታዲያ በትውልድ ቅብብሎሽ እዚህ ደረጃ ደርሶ አሁንም ተጠናክሮ ቀጥሏል። ይህንኑ እሴት ተከትለው አረጋውያንን፣ የአእምሮ ህሙማንን፣ የተለያዩ ችግሮች የገጠሟቸው ሴቶችንና ወላጅ አልባ ሕፃናትን የሚረዱ በጎ አድራጎት ድርጅቶችም በተለያዩ ጊዜያት ተቋቁመው ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ይገኛሉ።

ከነዚህ ውስጥም እንደነ ሜቄዶንያ፣ ሙዳይ፣ ጌርጌሲኖንና ሌሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንም በዋቢነት መጠቀስ ይቻላል። እነዚሁ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በየጎዳናው የወደቁ አረጋውያንና የአእምሮ ህሙማንን በማንሳትና በመንከባከብ በገንዘብ ሊተመን የማይችል ትልቅ ሰብአዊ ድጋፍ ፈፅመዋል። በተለያዩ ምክንያቶች ለችግር ለተጋለጡ ሴቶችና ወላጅ አልባ ለሆኑ ሕፃናትም ጥላ ከለላ ሆነዋል። በዚሁ ሰብአዊ ተግባር ሌሎችም እንዲሳተፉም ትልቅ አርያ ሆነዋል።

እምብዛም አልታወቁም እንጂ በየመንደሩና በየሰፈሩ ተመሳሳይ የሰብአዊ ድጋፍና እንክብካቤ የሚያደርጉ ማህበራትና በጎ አድራጎት ድርጅቶች አልጠፉም። በአዲስ አበባ ከተማም በተለያዩ አካባቢዎች ወጣቶች የበጎ አድራጎት ማህበራትን በማቋቋም በአካባቢያቸው በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙና አቅመ ደካማ ሰዎችን በተለያዩ መንገዶች በመርዳት ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ይገኛሉ።

ይህ አርያነት ያለው የወጣቶች ተግባር ታዲያ በተለይ ደግሞ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ በጉልህ ታይቷል። በርካታ ወጣቶችም የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ገቢያቸው አነስተኛ በሆኑ የአካባቢያቸው ነዋሪዎች ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ተፅእኖ አስቀድመው በመገመት ከኪሳቸው አውጥተው፣ የአካባቢያቸውን ሰዎች ለምነውና ሌሎች የግል ድርጅቶችን አስቸግረው ዘይት፣ ስኳር፣ ፓስታ፣ ሩዝ፣ ስንዴ እና ሌሎችንም የምግብና የፍጆታ ዕቃዎችን አሰባስበው ለግሰዋል።


በዚህ በጎ ተግባር ተሳትፈው የአካባቢያቸውን አቅመ ደካማና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰዎችን ከረዱና አሁንም እርዳታ እያደረጉ ካሉ አዲስ አበባ ውስጥ ከሚገኙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች መካከል አንዱ «የላምበረት ልጆች ለላምበረት ነዋሪዎች» በሚል መርህ የተመሠረተው የላምበረትና አካባቢው ለወገን ደራሽ የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው።

አቶ ደጉ መኮንን የላምበረትና አካባቢው «ለወገን ደራሽ በጎ አድራጎት ድርጅት» ዋና ሥራ አስኪያጅ ነው። እርሱ እንደሚለው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ከመመስረቱ በፊት የላምበረትና አካባቢው ወጣቶች በራሳቸው ተነሳሽነት አቅመ ደካማና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን አረጋውያን ይረዱ ነበር።

ይሁንና በመጋቢት ወር 2012 ዓ.ም የኮሮና (ኮቪድ-19) ወረርሽኝ ወደ ኢትዮጵያ በተከሰተ ወቅት የላምበረትና አካባቢው ለወገን ደራሽ በጎ አድራጎት ድርጅት በሚል ሕጋዊ ሰውነት ይዞ በሰባ አባላት ተመስርቷል። ድርጅቱ የተቋቋመበት ዋነኛ አላማም በተለያዩ ምክንያቶች ታመው አልጋ ላይ የቀሩ፣ አቅመ ደካሞችንና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የላምበረትና አካባቢውን ሰዎች ለመርዳት ነበር።

ድርጅቱ እንደተመሠረተም በላምበረትና አካባቢው የሚኖሩና በውጭ ኑሯቸውን ያደረጉ የላምበረት ተወላጆች ጋር በመተባበር በአካባቢው ላይ ረጅም ጊዜ የኖሩ፣ ተጠግተው የሚኖሩና አቅመደካማ የሆኑ ሰዎችን በገንዘብና በቁሳቁስ መርዳት ጀመረ። በተለይ ደግሞ ወቅቱ የኮሮና ወረርሽኝ የተከሰተበት ጊዜ እንደመሆኑ ድርጅቱ አባላቱ ገንዘብ እንዲያዋጡ በማድረግና በውጭ አገራት ያሉትም ገንዘብ እንዲልኩ በማድረግ አቅመ ደካማ ለሆኑና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የአካባቢው ነዋሪዎች ድጋፍ አድርጓል።

ድርጅቱ በወቅቱ ያደረገው ድጋፍም በአብዛኛው የምግብና የቁሳቁስ ነበር። ከእነዚህ ውስጥም ምግብ ነክ የሆኑት እንደ ዘይት፣ ስኳር፣ ፓስታ፣ ማካሮኒ፣ ዱቄትና



ፎቶ፡- በአስናቀ ፀጋዬ

አቶ ደጉ መኮንን፤

> የላምበረትናአካባቢውለወገንደራሽበጎአድራጎት ድርጅት እየፈፀመ ያለው በጎ ተግባር በአርያነት የሚጠቀስ ነው። በተለይ ወጣቶች ከዚህ ትልቅ ትምህርት ወስደው በአካባቢያቸው የሚገኙ አቅመ ደካሞችንና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ሰዎች በጉልበታቸው፣ በገንዘባቸውና በእውቀታቸው ለመርዳት እንደሚነሳሱ ይጠበቃል

የመሳሰሉት ይገኙበታል። ምግብ ነክ ካልሆኑት ውስጥ ደግሞ እንደ ሳሙና፣ ሶፍትና የመሳሰሉትን ለተረጂዎች አበርክቷል።

ሥራ አስኪያጁ እንደሚለው የኮሮና ወረርሽኝ ወደ አገሪቱ እንደገባ የድርጅቱ አባላት ከአምስት እስከ አስር ሺህ ብር በመዋጣት እርዳታ ጀምሯል። ይሁንና የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የመጀመሪያውን እርዳታ ከጨረሰ በኋላ እርዳታው ዘላቂ እንዲሆንና ሁልጊዜ መዋጮ እንዲኖረው በሚል በውጭ የሚኖሩ የላምበረት ተወላጆች በየስድስት ወሩ ስድስት ሺህ ብር እንዲያዋጡ ወስኖ በዚህ መልኩ መዋጮው እየተሰበሰበ ይገኛል። በተመሳሳይ እዚሁ ላምበረት የሚኖሩ የድርጅቱ አባላት ደግሞ ከሃምሳ ብር ጀምሮ እንደየአቅማቸው ለድርጅቱ በየወሩ መዋጮ ያደርጋሉ።

የበጎ አድራጎት ሥራው በድርጅቱ በኩል ሲጀመር በአገር ውስጥና በውጭ ከሚገኙ አባላት ከ300ሺህ ብር በላይ የተሰበሰበ ሲሆን በዚሁ ገንዘብ ምግብ ነክ የሆኑና ያልሆኑ ቁሶችን በመግዛት 300 የሚሆኑ የላምበርትና አካባቢው አቅመ ደካማና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎችን መርዳት ተችሏል።

የላምበረትና አካባቢው ለወገን ደራሽ የበጎ አድራጎት ድርጅት በአሁኑ ጊዜ አባላቱ የየራሳቸውን ሥራ በግላቸው ያከናውናሉ። ሆኖም በዚህ ድርጅት አማካኝነት የአካባቢው ወጣት አንድ ሆኖ ወርሃዊ መዋጮ በማድረግ አቅመ ደካማና በኑሮ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ የአካባቢው ነዋሪዎችን ይረዳል። ድርጅቱ ለነዚህ ሰዎች ርዳታ የሚያደርገውም በአብዛኛው አመት በዓልን አስታኮ ነው። ባለፈው የፋሲካና የኢድ በአላት ወቅትም ድጋፍ አድርጓል። በሌላ በኩል ደግሞ አዲስ አመት ሲመጣ በገቢ ዝቀተኛ ቤተሰብ ላላቸው ተማሪዎች የመማሪያ ቁሳቁሶችን ይረዳል።

የድርጅቱ አባላት በአሁኑ ጊዜ ሰባ የሚጠጉ ሲሆን በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የሚኖሩት የሚጠበቅባቸውን የአባላት መዋጮ እንደየአቅማቸው በየስድስት ወሩና በየወሩ ያዋጣሉ። ከእነዚሁ አባላት የሚሰበሰበው መዋጮም ለአካባቢው አቅመ ደካማና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላሉ ነዋሪዎች እርዳታ ይውላል።

ቅድሚያ የሚረዱትም ታመው አልጋ ላይ የዋሉ፣ በህመም ምክንያት መንቀሳቀስና ሥራ መሥራት የማይችሉ፣ አቅመ ደካሞችና ገቢ የሌላቸው አረጋውያን ናቸው። እርዳታው የሚሰጠውም በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ ዘጠኝ ከአራራት ሆቴል እስከ እስራኤል ኤምባሲ ባለው አካባቢ ለሚኖሩ ተረጂዎች ነው።

ከተቋቋመ ሦስት አመታትን ሊደፍን የተቃረበው የላምበረትና አካባቢው ለወገን ደራሽ ድርጅት የራሱ መሰብሰቢያ ቦታና ቢሮ እንደሌለው የሚናገረው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ፤ የድርጅቱ አባል የሆኑ አንድ ግለሰብ መገናኛ አካባቢ ያለውን ቢሯቸውን በበጎ ፍቃደኝነት ሰጥተውት እየተገለገለበት እንደሚገኝ ይገልፃል። ድርጅቱ የቢሮ ችግሩ ቢቀረፍለት ለዚህም ደግሞ ወረዳው ድጋፍ ቢያደርግለት ከዚህም በላይ ለአካባቢው ነዋሪዎች ትልቅ አስተዋፅኦ ሊያደርግ እንደሚችል ይጠቁማል። ይህንኑ ችግሩን ለወረዳ ዘጠኝ አስተዳደር በተደጋጋሚ አሳውቆ እንደነበርና ነገር ግን እስካሁን ድረስ በቂ ምላሽ እንዳላገኘም ይጠቅሳል።

‹‹እንደ በጎ አድርጎት ድርጅት እዚህ ደርሰናል፤ ነገ ደግሞ ድርጅቱ አድጎ የተሻለ ነገር እንዲሠራ በተለይ የየካ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ ዘጠኝ አስተዳደር ከድርጅቱ ጎን ነውና ወደ ፊትም ድርጅቱ ለሚያስፈልገው ድጋፍ ሁሉ ከጎኑ እንደሚሆን አልጠራጠርም›› ይላል ሥራ አስኪያጁ አቶ ደጉ መኮንን። ድርጅቱ ያሉበት ችግሮች ቢቀረፉ እኛም ትልቅ ደረጃ ላይ እንደርሳለን ብዬ አስባለሁ ሲልም ስሜቱን ይገልፃል።

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ ከተከሰተ ወዲህ የአካባቢውን አቅመ ደካማና አነስተኛ ገቢ ያላቸውን ነዋሪዎች እየረዳ የሚገኘው የላምበረትና አካባቢው ለወገን ደራሽ በጎ አድራጎት ድርጅት በቀጣይ እርዳታውን በስፋት ማዳረስ እንደሚፈልግ ሥራ አስኪያጁ ይገልፃል። የተረጂዎችን ቁጥር በማሳደግ የሚያደርገውን እርዳታ መጠንና ዓይነት የመጨመር ሃሳብ እንዳለውም ይናገራል።

ከእርዳታው ባሻገር ድርጅቱ የተለያዩ የስፖርት ማዘውተሪያዎችን በአካባቢው ላይ በመገንባት ወጣቶች አልባሌ ቦታ እንዳያሳልፉ የማድረግ አላማን ይዞ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝም ያስረዳል። ከዚህ አኳያ አንዳንድ እንቅስቃሴዎችን መጀመሩንም ሥራ አስኪያጁ ይጠቅሳል።

የላምበረትና አካባቢው ለወገን ደራሽ በጎ አድራጎት ድርጅት እየፈፀመ ያለው በጎ ተግባር በአርያነት የሚጠቀስ ነው። በተለይ ወጣቶች ከዚህ ትልቅ ትምህርት ወስደው በአካባቢያቸው የሚገኙ አቅመ ደካሞችንና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ሰዎች በጉልበታቸው፣ በገንዘባቸውና በእውቀታቸው ለመርዳት እንደሚነሳሱ ይጠበቃል።

አቶ ደጉ መኮንንም ወጣቱ ልስራ ካለ ጉልበቱም፣ እውቀቱም ሆነ ገንዘቡም እጁ ላይ ያለ በመሆኑ ነገ ዛሬ ሳይል ባለው አቅም ሁሉ በአካባቢው የሚገኙ አቅመ ደካማና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ሰዎች ለመርዳት እንደማይቸገር ይገልፃል። ሁሉም ወጣት በየአካባቢው እንዲህ ዓይነቱን በጎ ተግባር ቢፈፅም ችግሩን ሙሉ በሙሉ ባይቀርፍ እንኳን ችግሩን ለመቅረፍ የበኩሉን አስተዋፅኦ ማበርከት እንደሚችልም ይናገራል።

እንዲህ ዓይነቱን በጎ ተግባር የላምበረትና አካባቢው ለወገን ደራሽ በጎ አድራጎት ድርጅት የጀመረው ከሌሎች ተመሳሳይ ድርጅቶች ተሞክሮ በመውሰድ መሆኑንም ገልፆ፤ በተመሳሳይ የሌሎች የከተማዋ ነዋሪዎችም ከ’ኛም ሆነ ከሌሎች ተሞክሮውን ወስደው ሰዎችን ይርዱ ይላል። ይህን ማድረግ ከቻሉ የአእምሮ እርካታ ከማግኘት በዘለለ ማህበራዊ ኃላፊነትን የመወጣት ስሜትም እንደሚሰማቸው ይገልፃል።

እኛም የላምበረትና አካባቢው ለወገን ደራሽ በጎ አድራጎት ድርጅት ‹‹የላምበረት ልጆች ለላምበረት ነዋሪዎች›› በሚል እያከናወኑ ያሉትን በጎ ተግባር እያደነቅን በሌሎች የከተማዋ አካባቢዎችም ሆነ በሌሎች የክልል ከተሞች የሚገኙ ወጣቶች ከዚህ ተግባር በመማር ተመሳሳይ አርያነት ያለው በጎ ተግባር እንደሚፈፅሙ እናምናለን። ሰላም!!

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## በ“አንዲ ማማ“ - ወጣቶች ስለ ወጣቶች

ሰላማዊት ውቤ


ወጣት ብርቱካን አድማስ


ወጣት መቅደስ ተሾመ


ወጣት አንዱዓለም ኃብተ ጎርጊስ


ወጣት ምዕራፍ ገ/እግዚአብሄር


ከአንዲ ማማ ምርቶች


ወጣት የሺሀረግ ፍትጉ

ከአፍሪካ ሕዝብ 77 በመቶው ዕድሜው ከ35 ዓመት በታች የሆነ ወጣት መሆኑን በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ። እንደኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታም የወጣቱ ቁጥር ከዚህ አይተናነስም። የወጣቱ ቁጥር እንደ ብዛቱ በአንድ አገር ላይ ያለው አስተዋፅኦም የጎላ ነው። የወጣቱ ችግርም በሥራ አጥነት ከመሰቃየት ጀምሮ በርካታ ነው። የሴት ወጣቶች ችግር ደግሞ በእጅጉ ያይላል።

በተለይ ሴት ወጣቶች ገና በታዳጊነታቸው፣ በ10ና 15 ሲጋ ዕድሜያቸው ከማግባት ጀምሮ አባት የሌለው ልጅ የማሳደግ ሃላፊነት ይወድቅባቸዋል። ወንዱም ሆነ ሴቷ የመማርና ተምረው የመሥራት ዕድሉን የሚያጡበት ጊዜ ቀላል አይደለም። ሆኖም በተፈጥሮና በማህበረሰቡ ዘንድ ለሴትነት ካለው አመለካከት ጋር ተዳምሮ በሴት ወጣቶች ላይ የሚያርፈው ጫና ይበዛል። እንደ “አንዲ ማማ” አይነት ድርጅቶች ደግሞ እነዚህን መሰል ችግሮች ለመፍታትና የወጣቶችን ሸክም ለማቃለል የተፈጠሩ ናቸው።

ገቢያቸው በወር ከሁለት ዶላር ወይም ከመቶ ብር በታች የሆነና ይሄንንም የማግኘቱ ዕድል የሌላቸውን እናቶች ያቀፈው “አንዲ ማማ” ስለወጣቶች ችግርም ግድ ብሎታል። አምስቱ የአንዲ ማማ መሥራቾች በዕድሜ ከ20 እስከ 35 ዓመት መሆናቸው የበለጠ አግዟቸው ነው ወደ ሥራ የገቡት።

እኛም ለዛሬ ወጣቶች አብዝተው ስለራሳቸው በሚያስቡበት ዕድሜ ዘመን ላይ ቢሆኑም ስለ ዕድሜ አቻዎቻቸው ማሰብ ግድ እንደሚላቸው የአንዲ ማማ ፕሮጀክት መሥራቾቹ ወጣቶች አርአያ ይሆናሉ በሚል በጎ አሳቢ ወጣቶቹንና የበጎ ዓላማ ተጠቃሚ ወጣቶችን ተሞክሮ ልናጋራችሁ ወድደናል።

ወጣት አንዱዓለም ኃብተጊዮርጊስ የ”አንዲ ማማ” ፕሮጀክት ሊቀመንበር ነው። እንደገለፀልን ከሆነ ምንም እንኳን ፕሮጀክቱ እናቶች ላይ ቢያተኩርም፤ እናቶች የሚኖሩት ለልጆቻቸው እንደመሆኑ ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩና እንዲያበቁ የሚያስችል አቅም እንዲገነቡ ማስቻል ነው ዋና ዓላማው። አገር ውስጥ ያለውን የእናቶችን ችግር በጥልቀት መረዳትን መነሻ አድርገው የመሰረቱት ይሄው ፕሮጀክት እናቶችን ይንከባከባል። ለትርፍ እንደመቋቋሙም መልሶ ወረቀትን በመጠቀም ተግባሩ ለበርካታ ወጣቶች በተለያየ መልኩ የስራ ዕድል እየፈጠረም ይገኛል።

እንደ አንዱዓለም ገለፃ ወጣቶቹ ስለወጣቱ እንዲያስቡ ያደረጋቸው መነሻ ትምህርት ጨርሶ ሥራ ዕድል አጥቶ ሲንከራተት ከማየታቸው ጀምሮ ዘርፈ ብዙ ነው። የሚበሉትና የሚኖሩበት አጥተው ሌላው ቀርቶ የሚለብሱት ሁሉ አጥተው ትምህርታቸውን የሚያቋርጡ ወጣቶች መኖራቸው ቀደምና ጠለቅ ያለ የትምህርትና የሥራ ግንኙነት ለነበራቸው የአንዲ ማማ መሥራቾች ስለወጣቱ ችግርም በየፊናቸው በጥልቀት እንዲያስቡ መነሻ ሆኗቸው ቆይቷል። የቀደመ ትውውቅ ያላቸው እንደመሆናቸው ታዲያ ሰብሰብ ብለው በየውስጣቸው ስለወጣቱ ችግር እንዲወያዩ አደረጋቸው።

በተለይ ወጣት አንዱዓለም በአንድ ትምህርት ቤት ከጓደኞቹ ጋር ኳስ በሚጫወትበት ጊዜ የሰማውና ያየው ልቡን ነካው። ለተጫወቱበት ሜዳ መክፈል ግድ ነውና ለተጫወቱበት ሜዳ ለመክፈል የትምህርት ቤቱን አመራሮች ይጠይቃሉ። እናቶቻቸው ኑሮ ከብዷቸው ምግብ መብላት የማይችሉ ተማሪዎች አሉና ለእነዚህ በወር 400 ብር ስጧቸው ብለው ይመልሱላቸዋል። “እንዴት አንድ ተማሪ 400 ብር አጥቶ ምግብ ሳይበላ ይውላል? አንድ እናትስ እንዴት ይሄን የገዛ ልጇን መመገብ የሚያስችል አቅም እንኳን ታጣለች?” የሚለው መነሻ ሆናቸውና “አንዲ ማማ” ፕሮጀክትን መሰረቱ።

የእነዚህን ታዳጊ ወጣቶች እናቶችን ብናበለፅግ ልጆቹም ይበለፅጋሉ የሚል ዕይታ ተይዞም “አንዲ ማማ” ጥቅም ላይ የዋሉ ወረቀቶችን ሰብስቦና መልሶ ጥቅም ላይ ለሚያውሉ አካላት ወደ ማቅረብ ሥራው ተገባ። አምስቱ ወጣቶች የእናትን ድንቅነት ያነገበው ሀሳብ ቀድሞ በየውስጣቸው ይብላላ የነበረ ነበርና ተግባብተውበት ለመጓዝ ችግር አልነበረባቸውም። በዚህ ላይ ቀድሞ ትውውቅ ነበራቸውና ሀሳቡን በጋራ አዳብረውት ፈጥነው ነው ወደ ሥራ የገቡት። ወደ ሥራ ከገቡ አንድ ዓመት ከአራት ወራቶች አስቆጥረዋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ጋዜጦች፣ መጽሔቶችና መጻሕፍትን ጨምሮ በብዙ ቶን የሚቆጠሩ የተለያየ ቀለም ያላቸውንና የሌላቸውን ወረቀቶች ከየተቋማቱ በመሰብሰብ በመልሶ ጥቅም ላይ ለሚያውሉ አካላት ማቅረብ ችለዋል። ወረቀት የሚገኝበት መንገድ ልክ ባለመሆኑ በተቋማት ዘንድ የባሕርይ ለውጥ ማምጣት የሚያስችል ግንዛቤ ፈጠራ ላይም ሲሰሩ ቆይተዋል። ግንዛቤው ወረቀትን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል በየጊዜው ሀገራችን ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ የምታስገባውን 200ሺህ ቶን ወረቀት የሚተካ ትልቅ ሀብት በመሆኑ ቆሼ መጣል፣ ማቃጠልና በውሃና በሌሎች ነገሮች ማበላሸት ተገቢ አለመሆኑን ማመላከት ላይ ያተኮረ ነበር። ወደ ትላልቅ ኢንዱስትሪ የሚለወጥና የገቢ ማስገኛ ምንጭ በመሆን እናቶችና ወጣቶችን የሚያበለፅግ ለመሆኑም ሥራቸውን ማሳያ አድርገው ሲያብራሩለት ነው የከረሙት።

ወረቀት በመሰብሰቡ፣ የተሰበሰበውን ወረቀት መልሶ እፁብ ድንቅ የሚባልላቸውንና የተዋቡ የቤት ውስጥና የቢሮ እንዲሁም ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰጡ ቁሳቁሶችን ጥቅም ላይ በማዋልና ለገበያ በማቅረቡ ለ63 እናቶች እንዲሁም ለ500ሺህ ወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠርና የገቢ ምንጭ ለማድረግም ሲሰሩበት ነው አንድ ዓመት ከአራት ወራቸውን ያስቆጠሩት። የወጣቶቹ ሥራ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የዕድሜ አቻዎቻቸውን ተስፋ አለምልሟል። በአንድ ዓመት ውስጥ 1ሺህ 50 እናቶችን፤ እንዲሁም 500ሺህ የዕድሜ አቻዎቻቸው የሆኑ ወጣቶችን ለመድረስ የሚያስችለውን ሀሳብ በእቅድ ደረጃ መሰነቅ አስችሎታል። በአንዲ ማማ እናቶችም፣ ወጣቶችም በዚህ ሥራ በተሳትፏቸው መጠን ገቢ ያገኛሉ። እናቶች በእናትነት አምባሳደርነታቸው ብቻ ቁጭ ብለው ይጠሩበታል። የሚያማምሩትና ዋጋቸው እጅግ ውድ የሆነውን እንደ አበባ ማስቀመጫ፣ መመገቢያና የመሳሰሉትን የቤት ውስጥና ሌሎች መገልገያ ቁሳቁሶችን በማምረቱ ሂደት እናቶች ብቻ ሳይሆን በርካታ ወንድና ሴት ወጣቶች ተሳታፊና ተጠቃሚ ሆነዋል።

የ29 ዓመት ወጣቷ ብርቱካን አድማስ እንዲህ ዓይነቱን የስራ ዕድል አንዲ ማማ ከፈጠረላቸው ወጣቶች መካከል አንዷ ነች። ብርቱካን በዚህ የወጣትነት ዕድሜ ዘመንዋ በበርካታ ነገሮች ተፈትናና ብዙ ውጣ ውረዶችን አሳልፋለች። ተወልዳ ያደገችው ደቡብ ጎንደር፣ ፋርጣ ወረዳ፣ ቱማቦ በሚባል አካባቢ ነው። ወደ አዲስ አበባ የመጣችው በ15 ዓመቷ ሲሆን ያመጣቻት አስተምራታለሁ ብላ አክስቷ ነበረች። ሆኖም የቤት ሰራተኛ አድርጋ ስላስቀረቻት የዚህ የዚህ በክፍያ አልሰራም ወይ በሚል በየሰው ቤት እየሰራች በማታው የትምህርት ክፍለ ጊዜ እስከ ስምንተኛ ክፍል እራሷን አስተምራለች። ሆኖም ጽኑ የትምህርት ፍላጎት ቢኖራትም በሰው ቤት ሥራ ከዚህ በላይ መማር አልቻለችም። ኑሮ ሲከብዳት በሕገወጥ ደላላ አማካኝነት ለሥራ ቤሩት ሄደች። ስትሄድ በቤት ውስጥ ሥራ ያጠራቀመችውን ብር ለሁለት ዓመት ቆይታዋ ግማሽ ክፍያ ዘጠኝ ሺህ ብር ከፍላ ነበር። ከሄደች በኋላም ቀሪውን ዕዳዋን ለሕገወጡ ደላላ ከፍላ ጨርሳለች። ሆኖም ሥራው ፍፁም አልተመቻትም። ዘጠኝ ሺህ ብሩን አገሬ ብሰራበትስ ብላም ተቆጭታ ነበር። ከማመናጨቅ ጀምሮ በስድብና ድብደባ የተሞላ በመሆኑ በአንድ ዓመት ከ10 ወሯ ጠፍታ ወደ አገሯ ተመለሰች።

ተመልሳ ስትመጣ ምነው ባልተመለስኩ እስከማለት የሚያደርስ ከበድ ከበድ ችግሮች ፈትነዋታል። ሥራ ከማጣት ባሻገር ለግለሰብ የምትከፍለው የቤት ኪራይ እስከማጣት ደርሳለች። ይሄም አንሷት ለልጇ የምትሰጠው ቁራሽ አጥታም ነበር። አንዲ ማማ የደረሰላት በዚህ ችግሯ ወቅት ነው። የኮልፌ ቀራኖዮ ክፍለ ከተማ ነዋሪ በመሆንዋ ወደ አንዲ የገባችው በወረዳው አማካኝነት በ”የደሃ ደሃ” ተመልምላ ነው። በአንዲ ማማ ታቅፋ መሥራት ከጀመረች ስምንት ወር ሆንዋታል። ወደ ሥራው የገባችው የአንድ ወር ስልጠና ወስዳ ነው። በወር ውስጥ መልሶ ጥቅም ላይ የሚውል ወረቀት ተመዝኖ ይሠጣትና ትጠቀልላለች። የመመገቢያ ሣህኖችና የቆሻሻ ቅርጫት እንዲሁም የተለያዩ ቁሳቁሶችን ትሰራለች። በወር እስከ 1ሺህ 500 ኪሎ የሰራችበት ወቅት አለ። በበኩልዋ የሥራ ዕድሉን በማግኘትዋ ወደ ተሻለ ሕይወት ተሸጋግሪያለሁ ብላ ታምናለች። ባለቤትዋ እያገዛት ጭምር በወር 2ሺህ ብር ለቤት ኪራይ እየከፈለች ልጅዋን ማስተማርና ማሳደግ ችላለች። አንዲ ታላቅ ራዕይ ይዞ በመነሳቱም ተስፋዋ በእጅጉ ለምልሟል።

ሌላዋ የ24 ዓመት ወጣት የሺሀረግ ፍትጉ ስትሆን በፕሮጀክቱ የሥራ ዕድል ያገኘች ነች። ከዚህ ዕድሜዋ ስምንቱን ዓመታት በሰው ቤት ሥራ ነው ያሳለፈችው። እንጀራ እናቷና አባቷ የራሳቸውን ኑሮ ነው የሚኖሩት። ሰው ቤት እየሰራች እስከ ስምንተኛ ክፍል ብትማርም ከባዱ የድህነት ጫና ከዚህ በላይ መግፋት አላስቻላትም። ምግብ ቀልፈውባት ሄዳው ምትፈልገውን ሳታገኝ ብዙ መከራዎችን በማለፍ ነው የእስካሁኑ ዕድሜዋን ያሳለፈችው። በሰው ቤት ሥራ ሁሉ ነገር ተቆጥሮና ተቆልፎ ነው የሚኬደው። በአንዲ ማማ ከታቀፈች ሰባት ወሯ ነው። አንድ ኪሎ ሲጠቀለል 100 ብር፤ ሲረከቡ ደግሞ 1ሺህ 200 ብር ይከፍሏቸዋል። በሚያዝያ ወር ብቻ 3ሺህ 700 ብር አግኝታለች። 2ሺህ 200 ብሩን ለቤት ኪራይ ትከፍላለች። ባለቤቷም ያግዛታል። ሆኖም አሁን ላይ ከቀድሞው በእጅጉ የተሻለ ኑሮ እየኖረች ነው።

ወጣት መቅደስ ተሾመ የአንዲ ማማ መሥራችና ምክትል ፕሬዚዳንት ናት።በአካውንቲንግ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ይዛለች። የተለያዩ የሙያ ትምህርቶችንም ተምራለች። ከትምህርት ቤት ስትወጣ ከተለያዩ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ተቀጥራ ስትሰራም ቆይታለች። መቅደስ በዚህ መካከል ነበር ውስጧ ሴቶችን አግዢ እያለ ለሚጠይቃት ጥያቄ መልስ መስጠት እንዳለባት ያሰበችው። በእሷ ዕድሜ ያሉ ወጣት ሴቶች ከራሳቸው አልፈው ሌሎችን ለማገዝ ብዙም ያሉበት የዕድሜ ደረጃ ይፈቅዳል ተብሎ ባይታሰብም ይሄንኑ በውስጧ ተፀንሶ ይወተውታት የነበረውን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ከቀሩት ከአራቱ የአንዲ ማማ መሥራቾች ጋር ተወያየችበት። አሁን ለሌሎች የዕድሜ አቻዎችዋ ሥራ በመፍጠርዋ እርካታ ይሰማታል።

ወጣት ምዕራፍ ገ/እግዚአብሄር የአንዲ ማማ መሥራችና የኮሚዩኒቲ ኢምፓወርመንት ምክትል ፕሬዚዳንት ናት። በዚሁ ዓመት 30ኛ ዓመቷን ትይዛለች። ወጣቷ በዋናነት የምትሰራው ሴቶች ላይ ሲሆን ሴቶች በኢኮኖሚ መብቃት አለባቸው የሚል ጽኑ አቋም አላት። ለቤተሰብና ለአካባቢ የሚደርሰው አንድ እናት ስትረዳ ነው። አንድ እናት ከቤት ተረዳች ማለት ሙሉ ቤተሰብ ተረዳ ማለት ነው። ይሄን በዋናነት ይዛ ምን ያህል እናቶችን ረዳች የሚለው ላይ ነው የምታተኩረው፤ እየተሯሯጠች ያለችው ይህንኑ ከማሳካት አኳያ ነው።

የአንዲ ማማ አባላት አሁን ላይ 63 እናቶችን በኢኮኖሚ እያበቁ ሲሆን መድረስ የሚፈልጉት 1ሺህ 50 እናቶችን ነው። እነዚህን መድረስ 1ሺህ 50 ቤተሰብ መድረስ ማለት። አንድ በኢኮኖሚ በቃች ማለት ከልጆችና ባሏ ጀምሮ ቤተሰብኗ ረዳች ማለት ነው። እዚህ ለመድረስ ጠንክረው እየሰሩ ነው። ፓኬጆቻቸው ለየትና በተን ያሉ ሲሆኑ አንደኛው እንደ ማርኬቲንግ አምባሳደርነታቸው እናቶች ምንም ነገር ሥራው ላይ ሳይገቡ ከቤታቸው ሆነው ይደገፋሉ። ወረቀት ከየተቋማቱ የሚሰበስቡ የጽዳት ሠራተኞችም እንዲሁ ደሞዛቸው ዝቅተኛ በመሆኑ የሚደገፉበት አለ። ‹‹ልንሰራበት ያሰብነው ነገር ሩቅ አይደለምፐ፤ አጠገባችን ነው ያለው›› የምትለዋ ወጣት ምዕራፍ በተለይ ትኩስ ጉልበቱም፣ ጊዜውም፣ ዕውቀቱም ያላቸው ወጣቶች ከዚህ አጠገባቸው ላይ ካለው ነገር ተነስተው፤ በተለይ ከችግር መውጫ ቀዳዳው የጠፋባቸውን የዕድሜ አቻ ወጣቶችን፤ በተለይም ሴቶችንና እናቶችን አካባቢውን ማገዝ እንደሚቻል “አንዲ ማማ”ን ማሳያ አድርጋ ሀሳቧን አሳርጋለች። ሰላም!

# የማዕድን ዘርፉን ለሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት

**ስምስም መንግሥቱ**

ኢትዮጵያ በ2012 ዓ.ም የማዕድን ሀብት ልማት ፖሊሲ ረቂቅ ማዘጋጀቷ ይታወሳል።ረቂቅ ፖሊሲው መነሻ ያደረገው የሀገሪቱን የማዕድን አለኝታና በዘርፉ ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶች ላይ እንደሆነ ይጠቁማል። በረቂቁ ላይ እንደሰፈረው እስከ 21ኛው ክፍለ ዘመን የዲጂታል ቴክኖሎጂ ድረስ ስኬቶችና ሀገራዊ አቅሞች እውን መሆን የቻሉት የጥሬ ማዕድን ሀብትን ለተለያዩ ዘርፎች በግብዓትነት በመጠቀም ነው። ወደ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ሲመጣ ደግሞ በሀገሪቱ ትርጉም ባለው ደረጃ ዘመናዊ የማዕድን ሀብት ልማት የሚታየው በወርቅ ደረጃ ነው። ይሁን እንጂ ይህን ልማት ወደ ሌሎች የከበሩ ማዕድናት የማስፋፋት ውስኑነቶች ይስተዋላሉ። የወርቅ ማዕድን ማውጣት ሥራም ቢሆን የረጅም ጊዜ ታሪክ ይኑረው እንጂ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ከማሳደግ፣ለዜጎች የሥራ ዕድል ከመፍጠር፣በገንዘብ ተቋማት ዋስትና ከመቆጠር፣በሀገር ደረጃ እንደ አንድ ኢንደስትሪ ተወዳዳሪ ሆኖ ጎልቶ ከመውጣት አንጻር ብዙ ርቀት መጓዝ አለመቻሉ በሰነዱ ሰፍሯል። ኢትዮጵያ ለወጠነችው መዋቅራዊ ሽግግር እቅድና የመካከለኛ ገቢ ትልም መሳካት ወሳኝ እንደሆኑ የታመነባቸውን የአምራች ኢንደስትሪና የግብርና ቴክኖሎጂን ከማፋጠን አንጻር ከማዕድን ልማት ገና ብዙ ሥራ ይጠበቃል።ዘርፉ በሌሎች ተቋማት ላይ እንደሚስተዋለው ሁሉ የአፈጻጸም ሥልትና የተቋማት ዝቅተኛ ብቃት እንዲሁም ተቀናጅቶ አለመሥራት ክፍተቶች እንዳሉበትም በሰነዱ ተወስቷል። የሥርዓት መለዋወጥም ልማቱ ቀጣይነት እንዳይኖረውና ትኩረትም እንዲያጣ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል ተጠቅሷል።

ኢትዮጵያ በመዋቅራዊ ሽግግር ሂደት በኢንዱስትሪ ልማት መበልጸግ ግብ አድርጋ ስትንቀሳቀስ ጥሬ ማዕድናትን ወይንም በከፊል የተሰናዱ የማዕድን ውጤቶችን በግብአትነት መጠቀሟ የግድ መሆኑም ተመልክቷል። በሀገር ውስጥ የሚገኙ ማዕድናትን ለግብአትነት መጠቀም አዋጭ ብቻ ሳይሆን፣የመዋቅራዊ ሽግግር የማይታለፍ እርከን መሆኑም በሰነዱ ተመልክቷል። ለቀጣዮቹ 20 አመታትም የማዕድን ዘርፍ ልማት ርዕይ ተቀምጧል። በእነዚህ አመታት ውስጥ የኢንዱስትሪ ልማት መሠረት የሚሆን ፍትሐዊና ዘላቂ ማህበራዊ ተጠቃሚነትን እንዲሁም ዘላቂ ልማትን የሚያረጋግጥ እንደዘርፍም ተወዳዳሪ የሆነ የማዕድን ኢንዱስትሪ አቅም መፍጠር አንዱ ሲሆን፣በሌላ በኩል ኢትዮጵያ መካከለኛ ገቢ ካላቸው መካከል አንዷ እንድትሆንና ለዚህም የሚመጥኑ አቅሞች ባለቤት ለመሆን እንድትበቃ ከተተለመው ርዕይ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማስቻል እንደሆነም ተጠቅሷል።

ኢትዮጵያ በማዕድን ዘርፍ ያላትን ሀብት የመለየትና በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ዘዴ የማጠናቀር የትኩረት አቅጣጫ የሆነውን የልማት ስትራቴጂዎችን ካላት ሀብት ጋር ማጣጣም መቻልን ፣ ለአምራች ኢንደስትሪ ልማትና ግብርናው እንዲዘምን የግብአት አቅሞችን ቀድሞ መለየት በማዕድን ዘርፍ ተወዳዳሪ ኢንዱስትሪ ለመገንባት፣አዋጭ መስኮች ለመለየትና በማዕድን ዘርፍ ልማት በሚደረግ ኢንቨስትመንት ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ ሥርዓት መዘርጋትን የመሳሰሉ ጉልህ ፋይዳዎች ታሳቢ ያደርጋል። ዝርዝር ሀሳቦችን ያካተተው ይህ ረቂቅ የማዕድን ሀብት ፖሊሲ ለመጽደቅ የመጀመሪያ ደረጃ ላይ ይገኛል።ማዕድን ሚኒስቴር የማዕድን ዘርፉን በአግባቡ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስችል ፖሊሲ እንዲረቅ ከማድረግ ጀምሮ በውስጣዊ አደረጃጀቱም አቅም ለመፍጠር የሰው ኃይልን ጨምሮ በተለያዩ አደረጃጀቶች መዋቅራዊ ለውጥ(ሪፎርም) በማድረግ፣የተቋሙንም ገጽታ በመለወጥ መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ የማዕድን ዘርፉ በሀገር የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ አስተዋጽኦው ከፍ እንዲል እየሰራ መሆኑን የሚኒስቴሩ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ወይዘሪት ፌቨን ተሾመ ገልጸውልናል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ለመጽደቅ መጨረሻ ደረጃ ላይ የሚገኘው የማዕድን ሀብት ልማት ረቂቅ ፖሊሲ፣አንዱ የማዕድን ዘርፉን የሚመለከት ሲሆን፣ሌላው ደግሞ የነዳጅ ሀብትን የሚመለከት ነው። በተለይም ማዕድንን የሚመለከተው ፖሊሲ ዘርፉ ወደፊት ሊደርስ የሚችልበትን የእድገት ደረጃ ጭምር የሚያመላክትና ትልቅ ተስፋ የተጣለበት ሲሆን፣ፖሊሲው ለህዝብ ተወካዮች ምክርቤት ቀርቧል።

ሚኒስቴሩ የማዕድን ልማት ፖሊሲ እንዲወጣ ከማድረግ ጀምሮ እየወሰዳቸው ስላለው የለውጥ እርምጃዎች ፣ እስካሁንም ባከናወናቸው ተግባራት ያስመዘገባቸውን ውጤቶችና በቅርቡ ደግሞ በደቡብ አፍሪካ ኢንቨስቲንግ ኢን አፍሪካ ማይኒንግ(investing in Africa Mining) በሚል መሪ ቃል በሚካሄደው ጉባኤ እንዲሁም የዚሁ መርሃ ግብር ቀጣይ በሆነው የካናዳ ጉባኤን በተመለከተና በአጠቃላይ በዘርፉ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን እንቅስቃሴ እንደገለጹልን፤ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸው ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ያላቸውን የማዕድን ልማት ሥራዎች ለይቶ እየሰራ ይገኛል። ከትኩረት አቅጣጫዎቹ አንዱ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በግዥ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን የማዕድን ግብአት በሀገር ውስጥ መተካት ሲሆን ፣ ሥራዎችም ተጀምረዋል። ለአብነትም ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች ለኃይል ግብአትነት የሚውለውን የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ በመተካት የውጭ ምንዛሪ ወጪን ለመቀነስ የተወሰደው እርምጃ ይጠቀሳል። በዘርፉ ለመሰማራት ፍላጎትና የገንዘብ አቅም ያላቸው ስምንት የውጭ ኩባንያዎች ሀብቱ በሚገኝባቸው የተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ተመቻችቶላቸው ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል። ኩባንያዎቹ ግዙፍና ከስድስት ቢሊየን ብር በላይ ካፒታል ያላቸው ናቸው። ግብአቱን በማምረት በሀገር የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦ በተጨማሪ ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር እገዛ ያደርጋሉ።ኩባንያዎቹ በዘርፉ መሰማራታቸው የውጭ ንግድ አቅም ለመፍጠርና ለማሻሻልም ሚና ይኖረዋል። ኢትዮጵያ የድንጋይ ከሰል ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት በየአመቱ ወደ 300 ሚሊየን ዶላር ታወጣለች።ይህን ወጪ ለማስቀረት ወይንም ለማዳን ብቻ ሳይሆን፣ግብአቱን ለውጭ ገበያ በማቅረብም የውጭ ምንዛሪ ገቢ ለማግኘት ታሳቢ ያደረገ ነው።በመሆኑ በሁለተኛው የትኩረት አቅጣጫ የወጪ ንግድን ማሳደግ ነው።

የማዕድን ዘርፍ የተረጋጋና ከፀጥታ ስጋት ነጻ የሆነ አካባቢን ይፈልጋል ያሉት ዳይሬክተሯ፤ኢትዮጵያ በውስጥና በውጭ በገጠማት የጦርነትና የተለያዩ ችግሮች ምክንያት በውጥረት ውስጥ ብትሆንም በማዕድን ዘርፉ አበረታች የሆኑ ውጤቶች እንደተመዘገቡ፣በተለይም በወርቅ ማዕድን በ2013 በጀት አመት ጥሩ የሚባል ገቢ ለሀገር ማስገኘት መቻሉን ጠቅሰዋል። በተያዘው በጀት አመትም ጥሩ ውጤት እንደሚመዘገብ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ያሳያል። በበጀት ዓመቱ የዘጠኝ ወር አፈጻጸም ከአምና ተመሳሳይ ወር ጋር ሲነጻጸር የ12 በመቶ ብልጫ ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

በሦስተኛ ደረጃ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በትኩረት እየሰራ ያለው የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት በቴክኖሎጂ የታገዘ ዘመናዊ አሰራር ሥርአት መዘርጋት ነው። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የጀመራቸውን የለውጥ እንቅስቃሴዎች ዘለቄታ እንዲኖራቸው ከማድረግ አንጻር ያለው የቁርጠኝነት ማሳያዎችን በተመለከተ ዳይሬክተሯ ለቀረበላቸው ጥያቄ ‹‹የተለያዩ መሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል። ለምሳሌ በሀገሪቱ የማዕድን ሀብቶች በስፋት የሚገኙት የፀጥታ ስጋት ባለባቸው አካባቢዎች ነው። ሆኖም ግን ሥራው አልተስተጓጎለም። የበለጠ ውጤታማ ለመሆን ሚኒስቴሩ ከፌዴራል ፖሊስ ጋር ስምምነት በማድረግ የማዕድን ፖሊስ ክፍል እንዲዋቀርና ትላልቅ በሚባሉ የማዕድን መገኛ ስፍራ የፀጥታ ኃይል ተመድቦ እንዲሰራ በማድረግ የፀጥታ ስጋት ለመቀነስ የሚያስችል እርምጃ ተወስዷል። ይህ በመሆኑም ቀደም ሲል በፀጥታ ሥጋት ሥራ አቋርጠው የነበሩ ኩባንያዎች ወደ ሥራ ተመልሰዋል።አዳዲስ ኢንቨስተሮችንም መሳብ ተችሏል። ሥራውን በማጠናከር በበለጠ መንቀሳቀስ እንደሚገባ በሚኒስቴሩ ግንዛቤ ተይዟል›› በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። የፀጥታ መዋቅሩ መኖር የሀገር ሀብትን አላግባብ የሚያባክኑ ህገወጦችን ለመከላከልም አጋዥ እንደሚሆን አመልክተዋል።



ወይዘሪት ፌቨን ተሾመ

እንደ ዳይሬክተሯ ማብራሪያ ፤ መንግሥት የትኩረት አቅጣጫ ብሎ ለይቶ በአስር አመት ውስጥ ለመተግበር በዕቅድ ከያዛቸው አምስት ምሶሶዎች የማዕድን ዘርፍ አንዱ በመሆኑ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸውም ይህንኑ መሠረት አድርጎ በትኩረት ነው ተግባሩን እየተወጣ የሚገኘው። በትኩረት ካከናወናቸው ተግባራት የሰው ኃይል የአቅም ግንባታ አንዱ ሲሆን፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ በተለይም የማዕድን ሀብቱ በስፋት በሚገኝባቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች ከሚገኙ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲዎች) ጋር አብሮ ለመሥራት እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል። የትምህርት ተቋማቱ በማዕድን ዘርፍ ላይ ያተኮሩ የትምህርት ክፍሎችን (ዲፓርትመንቶች) በመክፈት ሙያተኞችን እንዲያፈሩ ማስቻል፣ በሌላ በኩል ደግሞ በጥናትና ምርምር አበርክቶ እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። በዚሁ መሠረት የትምህርት ተቋማቱ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በትብብር የሚሰሩበት ሥርዓት ተዘርግቷል። በአሁኑ ጊዜም ቁጥራቸው ወደ 45 የሚሆኑ ተማሪዎች በትምህርት ላይ ይገኛሉ። ለግንባታ የሚውለው ማርብል የተባለው ግብአት ላይ ስልጠና ለመስጠት በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ የስልጠና ማዕከል ለማቋቋም የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ተደርሷል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የውስጥ አቅሙን በማጠናከር፣የሌሎችንም ባለድርሻ አካላት ትብብር በመጠየቅና በማሳተፍ በሀገር ውስጥ እያከናወነ ካለው እንቅስቃሴ በተጨማሪ በተለያዩ ሀገራት በሚካሄዱ ጉባኤዎች ላይ በመሳተፍ ኢትዮጵያ በማዕድን ዘርፍ ያላትን እምቅ ሀብት ለማስተዋወቅና በዘርፉ ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸውን ባለሀብቶችንም ለመሳብ ጎን ለጎን ጥረት እያደረገ ይገኛል። በቅርቡ በደቡብ አፍሪካና በካናዳ በተከታታይ የሚካሄድ ጉባኤ ይጠቀሳል።

እዚህ ላይ ዳይሬክተሯ በሰጡት ማብራሪያ፤በማዕድን ዘርፍ ላይ በደቡብ አፍሪካና በካናዳ በሚካሄዱ ጉባኤዎች ላይ በዓለም ላይ ስመጥር የሆኑ የማዕድን ኩባንያዎችና እምቅ ሀብቱ ያላቸው ሀገሮች የሚሳተፉበት፣ አንዱ ለሌላው ያለውን ተሞክሮ የሚያካፍልበት እና የገበያ ትስስርም የሚፈጠርበት መድረክ ነው። ኢትዮጵያም ሀብቷን ለማስተዋወቅና ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ይህን አጋጣሚ ትጠቀምበታለች። ባላቸው የማዕድን ሀብት ልማት ፖሊሲ፣ሀብቱን በማልማትና ከዘርፉ ገቢ በማግኘት ከኢትዮጵያ የተሻለ ተሞክሮ ካላቸው ሀገራትና ኩባንያዎች ጋር በመገናኘት ልምድ ትቀስማለች። ይህም በደቡብ አፍሪካ እና ከአንድ ወር በኋላ ደግሞ በካናዳ በተመሳሳይ ጉባኤ ይካሄዳል።ከሁለቱ ሀገራት ቀጥሎ ወደፊት የሚካሄደው የዓለም የማዕድን ጉባኤ ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲካሄድ ከወዲሁ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ምክክር ተጀምሯል።ጉባኤው በየአመቱ የሚካሄድ በመሆኑ ኢትዮጵያ ሦስተኛውን ዕድል አግኝታ እንድታዘጋጅ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ይጠቅሳሉ።

በዚህ ወቅት ባለሀብቱ ቢሰማራባቸው ተብሎ ቅድሚያ የተሰጣቸው የትኞቹ የማዕድን ዘርፎች ናቸው ተብለው ለተነሳው ጥያቄም ዳይሬክተሯ በሰጡት ምላሽ፤ እንደሀገር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥም ሆነ ግብርናውን ለማዘመን ማዳበሪያ ትልቁን ድርሻ የሚይዝ በመሆኑ ቅድሚያ ከተሰጣቸው መካከል ማዳበሪያ በሀገር ውስጥ እንዲመረት ነው። ለማዳበሪያ ግብአት የሚውል ፖታሽ የተባለው ማዕድን በተለይ በአፋር ክልል ውስጥ በስፋት የሚገኝ በመሆኑ ባለሀብቱ በዚህ ዘርፍ ላይ ቢሰማራ ይመረጣል። በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ የማዳበሪያ ዋጋ ከፍተኛ በመሆኑ ከሀገር የመግዛት አቅም በላይ እየሆነ ነው። ስለሆነም በሀገር ውስጥ እንዲመረት መደረጉ ተገቢ ነው። ይሄ ትኩረት ይሰጠዋል። ሌላው ትኩረት የተሰጣቸው ዘርፎች ለግንባታ ግብዓት የሚውሉ ማርብልና ሴራሚክስ ናቸው፡፡ የትኩረት አቅጣጫዎቹ በቅደም ተከል ቢጠቀሱም በአጠቃላይ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጪ ተደርጎባቸው ወደሀገር የሚገቡ ግብአቶች በሀገር ውስጥ ምርት እንዲተኩና ለውጭ ገበያም ቀርበው የውጭ ምንዛሪ ግኝትን እንዲያሳድጉ ነው የሚፈለገው። የማዕድን ዘርፉ ተነቃቅቶ በሀገር የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ሚና እንዲኖረው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የጀመረው እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ከቀጠለ የላቀ ውጤት እንደሚመዘገብና እንደሀገር የተያዘው የልማት ግብም እንደሚሳካ ተስፋ እናደርጋለን።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የአባቶች ወግ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ብስራት በተለያየ መልከኛ እርሳሶች ስዕል እየሳለ አባቱ ፊት ይንደፋደፋል። አጠገቡ አብሮት የሚጫወተው የፈረንጅ ውሻ ዝም ብለህ ተቀመጥ የተባለ ይመስል የብስራትን ድርጊት በተመስጦ ያስተውላል።

የብስራት አባት ጋሽ ተፈራ ርዕሱ የተሸፈነ መጽሐፍ እያነበቡ ከብስራትና ከውሻው ራቅ ብለው ተቀምጠዋል። ሁሉም በራሳቸው ተመስጦ ውስጥ ወድቀዋል፤ ብስራት በሚሞነጫጭረው ስዕል ላይ፣ ቡቺ ምኑም በማይታወቅ ደመነፍሳዊ ተመስጦ ውስጥ፣ ጋሽ ተፈራ በሚያነቡት መሳጭ ታሪክ ውስጥ ራሳቸውን ጥለዋል።

ታዳጊው ብስራት ሳያስበው ወደ አባቱ ቀና አለ። የጀመረውን ሳይጨርስ ሀሳቡን ለሌላ ነገር የማይገብር የሕፃን አዋቂ ዓይነት ነበር፤ ዛሬ ግን በአባቱ ሀሳቡ ተሰረቀ። አባቱን እያስተዋለ ብዙ ቆየ። ማንንም እንደዛ አይቶ፣ በማንም እንደዛ ተመስጦ አያውቅም።

የሁልጊዜ የነፍሱ መመሰጫ በቴሌቪዥን የሚያያቸው የአሻንጉሊት ፊልሞች ነበሩ። ዛሬ ግን በአባቱ ተመሰጠ፤ በልጅነት ነፍሱ ውስጥ የሚያስገርም ትንሽዬ ግርምት ተጸነሰ። አባቱ አሁን የሚያነቡትን መጽሐፍ ይዘው ለዘላለም አይቷቸዋል። በልጅነት አእምሮው ቆጥሮ ለማይደርስበት ጊዜ ሳሎንና፣ መኝታ ቤት፣ በረንዳና፣ ሰገነት ላይ አይቷቸዋል።

የማያልቅ መጽሐፍ ሆኖ ነው ወይስ የማያልቅ ታሪክ ይዞ? የማይገባ ፍልስፍና ተጽፎበት ወይስ ከራስ የሚያጣላ አፍዝ አደንግዝ አርፎበት? አንዱንም አያውቀውም ብቻ ነጋ ጠባ ከእንቅልፉ ሲነቃና መሽቶ ወደ ማደሪያው ሲያዘግም እንዲሁም ደግሞ በሰንበት ከአባቱ ጋር ሲሆን አባቱን ከዚህ መጽሐፍ ጋር ነው የሚያገኛቸው። ሲያድግ ለአባቱ ከሚያቀርብላቸው ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ ለምን ይሄን መጽሐፍ ደጋግመው ያነባሉ የሚል ነው። ያኔ ከአባቱ አፍ የሚሰማው መልስ ሁሌም ሲያስደንቀው የሚኖር ይመስለዋል። ግን የዚህን መጽሐፍና የአባቱን ቁርኝት ለማወቅ እስኪያድግ መጠበቅ አላስችል ብሎት አሁኑኑ መጠየቅ ፈለገ። የሚሞነጫጭረውን ስዕል ወደ ጎን ብሎ ወደአባቱ ተንደረደረ።

‹አባ! አለ..አባቱ ፊት ሳይዛነፍ ቆሞ።

‹አባቱ ከሚያነቡት መጽሐፍ ላይ ተገተው ቀና አሉ። ሕፃን ሆኖ አልተረዳውም እንጂ ፊታቸው አጠገባቸው የቆመውን ሰው ሲቆጣ ነበር። ማንም ከዚያ መጽሐፍ ላይ፣ ከዛ ታሪክ ላይ፣ ከዛ ተመስጦ ላይ እንዲያነቃቸው አይሹም። በሕይወታቸው ምህረት የሌላቸው ለሁለት ነገር ነው ከዛ መጽሐፍ ላይ ላነቃቸውና አገራቸውን ኢትዮጵያን በክፉ ላየባቸው።

‹አባ ይሄ ምንድነው? አለ ብስራት ወደ መጽሐፉ በእጁ እየጠቆመ።

ምን እንደሚሉት ግራ ገባቸው። ሊያወርሱት ከሚፈልጉት ታላቅ እውነት ውስጥ አንዱና ዋነኛው ይሄ መጽሐፍና የዚህ መጽሐፍ ታሪክ ነው። አሁን ቢነግሩት የማይገባው ብዙ ነገር አለ..ሲያድግ ሁሉንም ሊነግሩት አስበው ነበር ግን ድንገት ጠየቃቸው። እስከሚያድግ ከሚጠብቁ እየነገሩት ቢያድግ ጥሩ እንደሚሆን በማሰብ ሊነግሩት ከወንበራቸው በመመቻቸት ጉሮሯቸውን አጸዳዱ።

‹የምነግርህን ነገር ለማመንና ለመቀበል፣ በዛ እውነት ውስጥ በታማኝነት ለመኖር ዝግጁ ነህ? ሲሉ ጠየቁት።

ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ።

‹እንግዲያውስ ይሄ መጽሐፍ አንተና ታሪክህ ነው። በየቀኑ የምታነበው፣ በየቀኑ የምታስበው፣ በየቀኑ የምትደነቅበት፣ በየቀኑ የምትመሰጥበት፣ በየቀኑ የምትኮራበት አንተና ታሪክህ ነው። ዘመንህን ሙሉ የምታነበው፣ ዕድሜህን ሙሉ የምትገልጠው፣ እስካለህ ድረስ የምታመሳጥረው አንተና ታሪክህ ነው። አሁን ላይ የምነግርህ ነገር ብዙም ላይገባህ ይችላል፤ ግን እየነገርኩህ እንድታድግ፣ እየነገርኩህ እንዳረጅ እፈልጋለሁ።

አልገባውም። በአባቱ ንግግር ትንሽ ነፍሱ ተፈተነች። አባቱ ዛሬ ገና አባቱ አልመስልህ አሉት። እንደዛሬ በማይገባው ቋንቋ የማይገባውን ነገር፣ በማይገባው ፊት ነግረውት አያውቁም።

ግራ እንደገባው ሲያውቁ «ልጄ አሁን አይገባህም፤ ግን እንዲህ እየተደናገርክ በልጅነትህ ውስጥ ታሪክህን እንድታበቅል እሻለሁ። ብዙዎች አድገው ኢትዮጵያ ማናት? ብለው ግራ ሲጋቡ አንተ ለራስህም ሆነ ለሌሎች ጥያቄ የሚሆን ብዙ መልስ ታገኛለህ። መደናገርህን አትጥላው። ከዚህ ሁሉ ግርታ በኋላ የምትደርስበት እውነት ስሩ የጠለቀ፣ ግንዱ የፈረጠመ፣ ቅርንጫፉ የትየሌለ የሆነ ነው። ከዛም አንተ በሌሎች ዛፍነት ውስጥ ዋርካ ይወጣህል፤ ሌሎች አንተን ለማጥላት አቅም ሲያጡ ታያለህ።

ይህ መጽሐፍ ይሄን ሁሉ የሚሰጥህን የኢትዮጵያውያንን ታሪክ የያዘ ነው። በሳይንሱም፣ በሃይማኖቱም ብትሄድ ፊተኝነት የእኛ ነው። ዓለምን የፈጠሩ እጆች የእኛ ናቸው። አድዋ በተባበረ ክንድ ታሪክህን ሲነግርህ በእዚህ መጽሐፍ ውስጥ ታገኘዋለህ። ለዛ ነው ዘመኔን ሙሉ ሳነበው የምታየኝ» ሲሉ ወደ ጉያቸው ስበው አቀፉት።

‹አባ ሳድግ ምንድነው የምሆነው?›

‹ስታድግ መሆን የምትፈልገውን አንተ ነህ መወሰን ያለብህ። እኔ በምትሄደው መንገድ አንተን መምራት ነው ድርሻዬ።

‹እኔ ግን..እንዳንተ መሆን ነው የምፈልገው...

‹እንደ እኔ ምን?

‹እንዳንተ ወንድ፣ እንዳንተ አባት፣ እንዳንተ ሰው፣ እንዳተ..

‹እንደ እኔ ከመሆንህ በፊት መጀመሪያ ራስን መሆን ይቀድማል። ምናልባት ራስህን ስትሆን ከኔ የተሻለውን አንተን ልታገኘው ተችላለህ። እንዳባት የምመክርህ መጀመሪያ ራስህን ከዛም እኔን እንድትሆን ነው›። ሲል ጉንጬን ሳመው። አጥብቆ ሲያየው ቆይቶ ‹ምትፈልገውን ለመሆን ጠንካራ ልብና አእምሮ ያስፈልግሃል።

‹ጠንካራ ልብና አእምሮ እንዴት ነው የሚገኘው? ልጁ የአባቱን ጎስቋላ አይኖች ሽቅብ እያስተዋለ ጠየቀ።

‹ጠንካራ ልብና አእምሮ የሚገኘው በጠንካራ ተስፋና ትጋት ነው። እጆችህን መስራት ስታስለምዳቸው፣ አእምሮህን ማሰብ ስታስተምረው፣ ልብህን ማፍቀር ስታለማምዳት፣ ነፍስህን ከኩነኔ ስታርቃት የኔ ጠንካራ ልብና አእምሮ ትሸምታለህ። ሰው ጠንክሮ ከሠራ መሆን የሚፈልገውን ሁሉ ይሆናል። የመከኑ ህልሞች፣ የራቁ ተስፋዎች በጠንካራ ትጋት ስላልፈለግናቸው የተሰወሩ ናቸው። አንተም ተስፋህን እንዳታርቅ፣ ህልምህን እንዳታዘገይ በትጋትና በትህትና የተገነባ ሰውነት ያስፈልግሃል›። ሳም አደረገው።

‹እኔ ግን እንዳንተ ነው መሆን የምፈልገው..› አለ ብስራት ለማኩረፍ በቃጣው ፊት።

‹እንደ እኔ መሆን ከፈለክም ከላይ በነገርኩህ የጥበብ መንገድ ላይ መራመድ ግድ ይልሀል። ወደ ከፍታ የሚያደርስህን የስብዕና ካባ መደረብ ይኖርብሀል። ካለ ዝቅታ የሚመጣ ከፍታ የለም፣ ካለ ጉስቁልና እፎይታ የማይታሰብ ነው፤ ወደ ፊት መሄድ ስታስብ በሕይወትህ ሁሌም ይሄን አስታውስ። ከሁሉ በላይ ደግሞ ሰው ሁን።

‹አሁንም እኮ ሰው ነኝ..

‹አዎ አሁንም ሰው ነህ ግን በአእምሮና ልብ ስትልቅ በአንተ ውስጥ የሚፈጠር ሌላ ሰው አለ።

ብስራት ግራ ገብቶት ዝም አለ።

‹ይሄን እውነት የምትደርስበት ነፍስህን ፍትህ፣ ልብህን ፍቅር፣ አእምሮህን ጥበብ ስታስተምራቸው ነው። ይሄን እውነት የምትረዳው በሰዎች ህመም መሰቃየት ስትችልና ራስህን ለሌሎች ስታብቃቃ ነው። ይሄን እውነት የምትረዳው ራስህን ስትሆን፣ ታሪክንህ ስታጠና፣ በዙሪያህ ያሉትን ስታፈቅርና የፈጠረህን ስትፈራ ነው› አሉት።

# ዓለም አቀፍ

## አብርሮ የማያውቀው ተሳፋሪ ፓይለቱ የታመመበትን አውሮፕላን በሰላም አሳረፈ

በአሜሪካዋ ፍሎሪዳ ግዛት አብራሪው መታመሙን ተከትሎ አንዲት አውሮፕላንን ያለምንም ችግር ማሳረፍ የቻለው ተሳፋሪ በበርካታ መገናኛ ብዙኃን መነጋገሪያ ሆኗል። ማንነቱን ለማጣራትም የዜና ወኪሎች ፍለጋ ላይ መሆናቸውም ተሰምቷል።

ማንነቱ ይፋ ያልተደረገው ይህ ተሳፋሪ በአየር ማረፊያው ከሚገኙ የበረራ ተቆጣጣሪዎች ጋር ያደረገው የድምጽ ልውውጥ እንደሚያሳየው ምንም አይነት አውሮፕላን የማብረር ልምድ የለውም። በድምጽ ቅጂው ላይ አውሮፕላኑን እንዴት ማሳረፍና ማቆም እንዳለበት እንደማያውቅ ሲናገር ይሰማል።

አዲስ አውሮፕላን አብራሪዎችን በማለማመድ የሚታወቅ አንድ የበረራ ተቆጣጣሪ ተሳፋሪው አውሮፕላኑን እንዲቆጣጠርና በሰላም እንዲያሳርፍ ሲረዳው እንደነበርም ተገልጿል። ይህ ክስተት ያጋጠመው ባለፍነው ማክሰኞ ዕለት ፓልም ቢች ዓለም አቀፍ ኤርፖርት ውስጥ ነው።ተሳፋሪው አውሮፕላኑን በሰላም ካሳረፈ በኋላ ከበረራ ተቆጣጣሪው ጋር መገናኘታቸው የተገለጸ ሲሆን ተቃቅፈውም ነበር ተብሏል።

"በጣም አሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለሁት። የአውሮፕላን አብራሪው ጥሩ ጤንነት ላይ አይገኝም። እራሱን ሳይስት አይቀርም" ሲል ይደመጣል በሬዲዮ ባስተላለፈው መልዕክት።በሬዲዮ አማካይነት አውሮፕላኗ በምን አይነት ሁኔታ ላይ እንደምትገኝ የተጠየቀው ተሳፋሪ ምንም የሚያውቀው ነገር እንደሌለና የፍሎሪዳ የባሕር ዳርቻን ከላይ እየተመለከተ እንደሆነ ተናግሯል።

"የአውሮፕላን ክንፎቹን አቅጣጫ አስተካክልና የባሕር ዳርቻውን ተከትለህ ወደ ሰሜን አልያም ወደ ደቡብ ዝም ብለህ አብርር። እኛ እናገኝሃለን" ሲል የበረራ ተቆጣጣሪው ነግሮት ነበር።አውሮፕላኗን ለማብረር የተገደደው ተሳፋሪ ደግሞ በምላሹ "የአቅጣጫ መቆጣጠሪያውን እንኳን ማብራት አልቻልኩም። እንዴት መቆጣጠር እንደምችል አላውቅም። እንዴት ማድረግ እንዳለብኝ ልትነግሩኝ ትችላላችሁ?" ሲል ይሰማል። አክሎም "አውሮፕላኑን እንዴት ማቆም እንዳለብኝ አላውቅም። ምንም የማውቀው ነገር የለም፤ እርዱኝ"



ብሏል በሬድዮ ባስተላለፈው መልዕክት።

ሮበርት ሞርጋን የተባለው የበረራ ተቆጣጣሪ ይህ ክስተት ባጋጠመበት ጊዜ እረፍት ላይ የነበረ ሲሆን፣ ባልደረባው ስለሁኔታው ሲነገረው በፍጥነት ወደ ሥራ ቦታው ተመልሷል።"አውሮፕላኗ ከሌሎች የተለየች እንዳልሆነች አውቃለሁ። ማድረግ የነበረብኝ አብራሪው ሳይደናገጥ ተረጋግቶ አውሮፕላኑን እንዲያበር መርዳት ነው። በሬዲዮ በኩል ኃይል እንዴት መቀነስ እንዳለበትና ወደ መሬት እንዲወርድ እንዲሁም እንዲያሳርፍ ረድቼዋለሁ" ብሏል።

በስተመጨረሻም አብራሪው አውሮፕላኗን በሰላም ማሳረፉን ሲነግረው በጣም እንደተደሰተና ማመን እንዳቃተው ለመገናኛ ብዙኃን ተናግሯል።ደፋሩ ተሳፋሪ አውሮፕላኗን በሰላም ካሳረፈ በኋላ ሮበርት ሞርጋን ወደ አውሮፕላን ማሳረፊያው በመሄድ እንዳቀፈውና ፎቶ አብረው እንደተነሱም ገልጿል። ነገር ግን በግርግር ውስጥ ስለነበረ ስሙን እንዳልሰማ ለመገናኛ ብዙኃን ገልጿል።

"ልክ በሰላም ሳገኘው እምባዬ መጥቶ ነበር። በጣም አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለፍነው። አብራሪው ምን ያክል ተጨንቆ ይሆን የሚለውን ሳስብ በእርጋታው በጣም ነው የተገረምኩት" ብሏል ከሲኤንኤን ጋር በነበረው ቆይታ።የአሜሪካ የአየር ትራንስፖርት አስተዳደር በበኩሉ ያለምንም አደጋ ማረፍ የቻለችው አውሮፕላን የግል እንደሆነችና ምንም አይነት አሳሳቢ ጉዳት አለመድረሱን ገልጿል።

በማብረር ላይ ሳለ የጤና እክል የገጠመው ካፕቴን አውሮፕላኗ በሰላም ካረፈች በኋላ ወደ ሆስፒታል መወሰዱን ቢቢሲ ዘግቧል።

## በአልቢኖ ግድያ የተሳተፉ ሦስት ግለሰቦች እያንዳንዳቸው የ155 ዓመት እስራት ተበየነባቸው

የማላዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አልቢኖ ያለበትን ግለሰብ የገደሉ ሦስት ሰዎችን እያንዳንዳቸውን በ155 ዓመት እስራት ቀጣ።የ44፣45 እና 71 ዓመት የሆናቸው ሦስቱ ግለሰቦች ባለፈው ጥር የ23 ዓመቱን ወጣት መግደላቸውን አምነዋል።

ከወንጀለኞቹ አንዱ የሟች አጎት ነው ተብሏል።ባለፉት አስር ዓመታት በማላዊ አልቢኖ (ተፈጥሯዊ የቆዳ ቀለማቸው ላይ ችግር የገጠማቸው) ያለባቸው ሰዎች ተደጋጋሚ ጥቃት እና ግድያ ሲደርስባቸው ቆይቷል።

ለዚህ ደግሞ ዋነኛው ምክንያት የሰውነት አካላቸው ጥሩ እድል እና ሃብት ያመጣል በሚል ሐሰተኛ እምነት ነው።አልቢኖ የቆዳ ቀለም በመንጣቱ ምክንያት የሚከሰት ሕመም ሲሆን በዘር የሚተላለፍ ነው። አልቢኖ ጥቁር ቆዳ ባላቸው ሰዎች ላይ በጣም ጎልቶ የሚታይ ቢሆንም ሁሉንም የሰው ልጆች ሊያጠቃ ይችላል።

ከቀናት በፊትም ከፍተኛው ፍርድ ቤት አልቢኖ ካለበት ግለሰብ ግድያ ጋር በተያያዘ የቀድሞ የሮማን ካቶሊክ ቄስ፣ የፖሊስ መኮንን እና የሕክምና ባለሙያ በሰው አካላት ንግድ ተሳትፈዋል በሚል ጥፋተኛ ብሏቸዋል። ይህም ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ በማኅበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ቦታ በሚሰጣቸው ግለሰቦች ላይ የተሰጠ ውሳኔ ነው ተብሏል።ውሳኔው እና የረዥም ጊዜ የእስር ቅጣቱ የፍትሕ አካላት በጥቃቶቹ እና በግድያዎቹ ዙሪያ ያላቸውን አቋም ያሳየ መሆኑን የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።



**ከኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም**

# የአስተዳደሩ የብቃት ማሳደጊያ ማዕከል

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የተቋሙን ሰራተኞች እና የመንገድ ልማት ዘርፉን ዋነኛ ባለድርሻ አካላትን የክህሎትና የዕውቀት ክፍተት በመለየት አጫጭር ስልጠናዎች አቅም ግንባታዎችን እያከናወነ ይገኛል። አስተዳደሩ ስልጠናዎችን የሚሰጥበት ሁለት ማዕከላት አሉት። እነሱም የአለምገናና የጊንጪ ማሰልጠኛ ማዕከል ናቸው:: የአገልግሎቱ ማሰልጠኛ ማዕከላት ዋነኛ ተጠቃሚዎች ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች፣ የግል ሥራ ተቋራጭ ኩባንያዎች፣ መንግስታዊ የኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዞች፣ የመንግስት ትላልቅ የግንባታ ፕሮጀክቶች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ግለሰቦች ናቸው። በዛሬው ዕትማችን የአለምገና ማሰልጠኛ ማዕከልን የምንቃኝ ይሆናል::

በ1943 ዓ.ም የተመሰረተውና 70ኛ ዓመቱን የተሻገረው የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር በአዋጅ ከተቋቋመ አምስት ዓመት በኋላ የአለምገና ማሰልጠኛ ማዕከል ተቋቁሟል። ማዕከሉ ከአዲስ አበባ በ19 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በዓለምገና ከተማ የሚገኝ ሲሆን በማሽን ቤዝድ ቴክኖሎጂ መካከለኛ ባለሙያዎችን ተቀብሎ ያሰለጥናል::

የአለምገና ማሰልጠኛ ማዕከል በአሁኑ ወቅት በአንድ ጊዜ የቅበላ አቅሙ እስከ 300 ሰልጣኞች አድርሷል። ማዕከሉ በየጊዜው የሚደረግ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናትን መሰረት በማድረግ የስልጠና ፈላጊዎችን የስልጠና ፍላጎት በዓይነትና በቁጥር በመለየት ዓመታዊ የስልጠና ፕሮግራም ያዘጋጃል። በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ለስልጠና ተጠቃሚዎች ያሠራጫል። ክልሎች እንዲያሰለጥኑ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ሲሆን በየሩብ ዓመቱ በማዕከሉ ምን ያህል ሰልጣኞችን ማሰልጠን እንደሚችሉ ኮታ ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም ከግል ኮንትራክተሮች፣ ከመንግስታዊ የልማት ድርጅቶችና በግለሰብ ደረጃ በማዕከሉ መሰልጥን የሚፈልጉ አካላት በአነስተኛ ክፍያ የስልጠና አገልግሎት ያገኛሉ።

ለስልጠና ከክልል ወደ ማዕከሉ የሚላኩ ሰልጣኞች ሙሉ የማረፊያና የምግብ (የቦርዲንግ) አገልግሎት



እያገኙ ስልጠናውን ይከታተላሉ:: የማዕከሉ ሰልጣኞች ስልጠናቸውን በተገቢው ሁኔታ ማጠናቀቃቸው ሲረጋገጥ፤ ገለልተኛ በሆኑ የብቃት ምዘና ማዕከላት ብቃታቸው እንዲረጋገጥ ይደረጋል። የብቃት ምዘናውን ያለፉ ሰልጣኞች የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ይሰጣቸዋል።

**የማሰልጠኛ ማዕከሉ ፋሲሊቲዎች**

- ❖ በአንድ ጊዜ 300 ሰልጣኞችን የማስተናገድ አቅም
- ❖ እያንዳንዳቸው ከ 40 እስከ 60 ሰልጣኞችን የሚይዙ የስልጠና ክፍሎች
- ❖ የተሟላ ላቦራቶሪ
- ❖ የመንገድ ግንባታ እና የሰርቶ ማሳያ ፕሮጀክቶች (ሳይቶች)
- ❖ የኦዲዮ-ቪዥዋል ዩኒት
- ❖ በአንድ ጊዜ እስከ 30 አንባቢያንን ሊያስተናግድ የሚችል ቤተ-መጽሐፍት
- ❖ ክሊኒክ
- ❖ የመመገቢያ አዳራሽ
- ❖ የመሰብሰቢያ አዳራሾች (ስማርት/ሲንዲኬት ክፍሎችን የያዙ)
- ❖ መለስተኛ ጋራዥ
- ❖ የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎችና የትራንስፖርት ማሰልጠኛ መሳሪያዎች ናቸው።

ማዕከሉ በሦስት ዋና ዋና ዘርፎች ሥልጠና የሚሰጥ ሲሆን እነሱም፡-

**በምህንድስና ዘርፍ**

- የኮንስትራክሽን ማቴሪያል ጥራት ቁጥጥር (MQC)
- በመንገድ ቅየሳ (Surveying Technology )
- የመንገድ ግንባታና ጥገና (Road construction & maintenance)

**በከባድ ኮንስትራክሽን ማሽነሪ ኦፕሬሽን ኦፕሬተርነት**

- በዶዘር ኦፕሬተር
- ግሬደር ኦፕሬተር
- የኤክስካቫተር ኦፕሬተር
- የሎደር ኦፕሬተር
- የሮለር ኦፕሬተር

**በከባድ ኮንስትራክሽን ማሽነሪ ጥገና**

- መካኒክ
- የተሽከርካሪ አካል ብየዳና ቅጥቀጣ
- ኤሌክትሪካል
- ማሽኒንግ/ሞዲፊኬሽን ናቸው።

ማሰልጠኛ ማዕከሉ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ለአገልግሎቱ የውስጥ ሠራተኞች በአምስት የስልጠና መስኮች ስልጠናዎችን ሲሰጥ ቆይቷል። በማዕከሉ ለአገልግሎቱ ሰራተኞች የሚሰጡ የስልጠና መስኮቹ የደረጃ ዕድገት፣ የሪፍሬሽመንት፣ የትውውቅ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ናቸው። ማዕከሉ ለሀገራችን የመንገድ ግንባታና ጥገና አፈፃፀም የራሱን ጉልህ ድርሻ አበርክቷል።

በተጨማሪም ማዕከሉ በአገልግሎቱ አዲስ ለሚቀጠሩ ጀማሪ መሐንዲሶች ከሥራው ጋር በፍጥነት ተላምደው ወደ ሥራ እንዲገቡ የሚሰጠውን የትውውቅ ሥልጠና ሂደት ከማስተባበር ጀምሮ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል። በመንገድ ግብዓት ጥራትና ቁጥጥር፣ በቅየሳ፣ በአውቶ ካድና ኢግል ፖይንት እና በመንገድ ሥራ ጥገና የትውውቅ ስልጠና ይሰጣል። በማእከሉ ለሚገኙ ሠራተኞች መሰረታዊ የኮምፒውተር ስልጠናም ይሰጣል።

የማሰልጠኛ ማዕከሉ የማዕከሉን ፋሲሊቲ ማሳደግ፣ የስልጠና ፕሮግራሞችን ማስተዳደር፣ የአሰልጣኞችን አቅም ማሳደግ፣ የሰልጣኝ ቅበላን/ቁጥር ለማሳደግ እና የስልጠና ስትራቴጂን እና ቀጣይነቱን በመከለስ ለመንቀሳቀስ ትኩረት በመስጠት እየሰራ ይገኛል:: በቀጣዩ ዕትማችን በ1972 ዓ.ም የተቋቋመውን የጊንጪ ማሰልጠኛ ማዕከል የምንቃኝ ይሆናል::

**አድራሻ**

Facebook: - Ethiopian Roads Administration

Telegram:-ERA ኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም**

# ሙያዊ የብቃት ምዘና ለመምህራንና ለትምህርት ቤት አመራሮች

**ወርቅነሽ ደምሰው**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት በመስጠት የኀብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካትና ተፈላጊውን ለውጥ ለማምጣት እየሰራ ነው። የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮችን ሙያዊ ብቃት ማረጋገጥ ወሳኝነት ያለው በመሆኑ ትኩረት ሰጥቶት በርካታ ሥራዎች እያከናወነ ይገኛል። በመሆኑም ለነባርና ወደ ሙያው ለሚገቡ ጀማሪ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራር ከትምህርት ይዘትና ከማስተማሪያ ስነዘዴ አንጻር የጽሑፍ እንዲሁም ለነባር መምህራንና የትምህርት ቤት አመራር የማህደረ ተግባር ምዘናዎችን በመስጠት ክፍተቶችን ማመላከት የሚያስችል ተግባራት እያከናወነ ይገኛል።

በዚህም መሠረት በዘንድሮ ዓመት በምዘና ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ መምህራንና የትምህርት አስተዳደር ሠራተኞች እንዲሁም ሱፐርቫይዘሮች እውቅና እና ሰርተፊኬት መስጠቱ ይታወሳል። ይህንን አስመልክቶ የያዝነውን ዝርዝር ያለ ማብራሪያ እንደሚከተለው ለማጋራት ወደድን። መልካም ንባብ።

የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ሙያ ፍቃድ ሥርዓት እንደ ሀገር በ2004 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን፤ የትምህርት ጥራት ውስንነት በመቅረፍ ብቁ ወይም ተወዳዳሪና ለሙያቸው የተሰጡ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች እንዲኖሩ ለማድረግ ያለመ ነው። የአዲስ አበባ ትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ምዘና ከጀመረ ከ2005 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም 17ሺ 849 የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን የሙያ ብቃት የጹሑፍ ምዘና ወስደዋል። ይህም ከአጠቃላይ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን ውስጥ (64 በመቶ) ያህሉን የሚያካትት ነው።

የባለስልጣኑ ጥናታዊ ጽሑፍ እንደሚያሳየው፤ የጹሑፍ ምዘና ከተመዘኑት 17ሺ849 መምህራን ውስጥ አምስት ሺ913 (33በመቶ ) በጹሑፍ ምዘናው ማለፊያ ውጤት (62ነጥብ 5 በመቶ እና ከዛ በላይ ) ማስመዝገብ የቻሉ ናቸው። እንዲሁም የጹሑፍ ምዘና ማለፊያ ውጤት ካመጡት መምህራን ውስጥ አራት ሺ534 (22በመቶ) የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት ችለዋል።

በተመሳሳይ 712 የትምህርት ቤት አመራሮች የሙያ ብቃት የጹሐፍ ምዘና የወሰዱ ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ የአዲስ አበባ ከተማ የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች አመራሮች 29ነጥብ አንድ በመቶ ያህሉ ናቸው።

የጹሐፍ ምዘና ከተመዘኑት 712 የትምህርት ቤት አመራሮች ውስጥ 218 (31በመቶ) በጹሑፍ ምዘናው ማለፊያ ውጤት (62ነጥብ5 በመቶ እና ከዛም በላይ ) ማስመዝገብ የቻሉ ናቸው። እንዲሁም የጹሑፍ ምዘና ማለፊያውን ካመጡት የትምህርት ቤት አመራሮች ውስጥ ውስጥ 190 (27በመቶ) የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ማግኘት መቻላቸው ተገልጿል።

የመምህራንም ሆነ የትምህርት ቤት አመራሮች የሙያ ብቃት የጹሑፍ ምዘና ውጤት የሚያሳየው ሌሎች ከምዘና መሳሪያውና በአተገባበሩ ላይ የመምህራኑ ሆነ የትምህርት ቤት አመራር በኩል ያሉ እጥረቶች እንዳሉ ሆኖ በመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ማብቃት ላይ ሥራዎች እንደሚያስፈልጉ ተስተውሏል።

በምዘናው ሂደት የታዩ መልካም አጋጣሚዎችና ምቹ ሁኔታዎች በርካታ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥም የእውቅና ፈቃድ መመሪያ መኖሩ፣እንደ ከተማ አስተዳደር የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች የሙያ ብቃት ምዘናውን ለማከናወን የሚያስችል በቂ በጀት የሚመደብ መሆኑ፤መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች በሙያ ብቃት ምዘና በማለፍ የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ፍላጎት እያሳዩ መሆን፤ በተለያዩ የግንዛቤ መስጫ መድረኮች እና በትምህርት ቤቶች በሚደረግ የክትትልና ድጋፍ ሥራዎች እና በምዘና ወቅት ከመምህራንና የትምህርት ቤት አመራር የተሰበሰቡ መረጃዎች የሚያሳዩት ለሙያ ብቃት ምዘና ፋይዳ በአብዛኛው አዎንታዊ መሆናቸው ተጠቅሷል።

በተግዳሮቶች ከተቀመጡት ውስጥ ደግሞ የሙያ ብቃት ሰርተፊኬት ያገኙንና ያላገኙን የሚለይ አሰራር ያለመኖሩ/የማበረታቻ ሥርዓት ያለመዘርጋቱ/፣መምህራን የሚሰለጥኑበት የስልጠና ሞዳሊቲ በየኮሌጁ የተለያየ መሆን፣ እንደ ሀገር ወጥ የሆነ አደረጃጀት ያለመኖሩ ፤ከትምህርት ቤቶች ጀምሮ ያለው የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ውስንነት ያለበት መሆኑ፤የምዘና ውጤቱን እንደ ግብአት በመጠቀም የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያለመስራት እና ከምዘናው ሂደትና ውጤት በመነሳት የሚታዩ ክፍተቶች ለመቅረፍ የባለድርሻ አካላት ትኩረት አናሳ መሆን (ከመረጃ ልውውጥ፤ ሰነዶችን መምህራን በተመሏ መልኩ እንዲጠቀሙባቸው ከማድረግ ፤ የምዘና ጣቢያዎችን ከማመቻቸት) ናቸው።

በተጨማሪም የግል ትምህርት ቤቶች መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች የደረጃ እድገት የሌላቸው መሆኑ፤ የማህደረ ተግባር የሚያደራጁበት እንቅስቃሴ ያለመኖሩ እና በርካታ የግል ትምህርት ቤት መምህራን የስነ ዘዴ ስልጠና ያልወሰዱ አለፍ ሲልም ከዘርፉ የተለየ ስልጠና የወሰዱ መሆናቸው ይጠቀሳል። በ2013 ዓ.ም ተቋሙ በሰበሰበው መረጃ 24 በመቶ መምህራን ባልሰለጠኑበት እየሰሩ የሚገኙ መሆኑ እና የመሳሳሉት ተጠቅሷል፡

በአዲስ አበባ በተለይ ከመንግሥት የትምህርት ተቋማት ይልቅ የግል የትምህርት ተቀማት ቁጥር ይበልጣል። በግል ትምህርት ቤቶች ያሉ የመምህራን ሙያዊ ስልጠና እንቅስቃሴዎች ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች ጋር ተጣጥሞ የሚሄድበት አሰራር እንዲኖር ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባል። የሙያ ብቃት ምዘና ውጤቶችን ለአቅም ግንባታ ሥራዎች እንደ ዋነኛ ግብአት አድርጎ መጠቀም መቻል የሚሉት የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል።

በአጠቃላይ በዘንድሮ ዓመት ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ «የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ብቃት ለትምህርት ጥራት» በሚል መሪ ቃል የመምህራንና የትምህርት አመራሮች የሙያ ብቃት ምዘና ይፋ ያደረገ ሲሆን ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡት እውቅና ሰጥቷል። በዚህም መሠረት ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ 377 መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች እውቅና መስጠቱ የሚታወስ ነው።

**አድራሻ**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን**

(City Government Of Addis Ababa Education and Training Quality Control Authority)

https;// www.facebook.com/AA-Educational-Training- Quality-Occ-Competency Assurance-Authority- 100864428091362/?_tn_=-UC*F

ድረ ገጽ፡- www.educoc.gov.et